ልማታዊነት ወይንስ ገበያ

የኢኮኖሚ ትንተና

ልማታዊነት ወይንስ ገበያ

ማቲያስ ገሠሠ

ሚያዚያ 25፥ 2018

ክፍል 1

ማውጫ

1 መግቢያ 1

2 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 5

2.1 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ የሚቀርብ "ክስ" 7

2.1.1 ከገበያው አንጻር ዝቅተኛ ወለድ ለሚከፍሉ መስኮች ከፍተኛ ብድር ይሰጣል 7

2.1.2 ሰፊ መጠን ያለውን የሐገሪቱን የቁጠባ ገንዘብ ከእላይ በተጠቀሰው መንገድ እማያዋጡ መስኮች በስፋት (በሙላት) ያበድራል 8

2.1.3 የውሸት የተበላሸ ብድር መጠን ስሌት 9

2.1.4 የካፒታል መቃብር ስፍራ ነው (የሚያበድራቸው ብድሮች የመክሰር ዕድላቸው ከፍተኛ ነው) 9

2.1.5 የገበያ ሳይሆን የፖሊሲ ብድር ያስከተለው ኪሳራ 10

2.1.6 ስኬትን የማጋነን አባዜ 11

2.1.7 የግብር ድጎማ ይቀበላል 12

2.1.8 ብቃት ያለው የካፒታል አደላደል አለኝ የሚል ቅዠት (THE CAPITAL ADEQUACY FICTION)13

2.1.9 ሞኖፖሊ 15

2.1.10 ካፒታል በማገት ጉዳት ያደርሳል 15

2.1.11 ለፖሊሲ ማበደር ያስከተለው የትርፍ መቀነስ 15

3 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በገበያ ቢሠራ 17

3.1 50% የባንኩን ድርሻ ከትርፍ የመካፈል መብት ጋር ለትልቅ የውጭ ባንክ መሸጥ 21

3.2 ባንኩ በሐገሪቱ የቁጠባ ሒሳብ ላይ ያለውን የበላይነት በሕግ መቀየር 21

3.3 የባንኩ ቦርድ ነጻ እና ገለልተኛ እንዲሆን 50% በግል ባለ ኃብቶቹ እንዲሰየም ማድረግ 22

3.4 ባንኩ በዓለም ላይ ካሉት አራት ዋነኛ ኦዲተሮች በአንዱ ኦዲት እንዲደረግ በማድረግ የባንኩን ግልጸኝነትን ማረጋገጥ 22

3.5 ከፍተኛ የባንኩ ተበዳሪ የሆኑትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለግል መሸጥ 22

3.6 ባንኩ የመንግሥትን ቦንድ በገበያ የወለድ መጠን እንዲገዛ ማድረግ 23

3.7 ከመንግሥት ቦንድ ግዢ የሚገኝ ገቢ እንደ ሌላ ማንኛውም ዓይነት ገቢ የመንግሥትን የገቢ ግብር እንዲከፍል ማድረግ 23

3.8 ባንኩ መንግሥት በቅርቡ ካቋቋመው የዕዳ እና የንብረት አስተዳደር ኮርፖሬሽን (Liability and Asset Management Corporation - LAMC) ጋር ያለው ግንኙነት በሕግ መቋረጥ አለበት 24

1 መግቢያ

ከ90% በላይ የእሚሆነው ኢትዮጵያዊ ፤ ኢትዮጵያ ኋላ ቀር ግብርና መር ከሆነ ኢኮኖሚዋ ተላቃ ፤ ኢንደስትሪ መር የሆነ ኢኮኖሚ ውስጥ በመግባት ወይንም በዘርፉ ቋንቋ መዋቅራዊ ሽግግር አድርጋ ፤ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የኑሮ ደረጃ ተሻሽሎ ፦ የነፍስ ወከፍ ገቢው ፣ ምርታማነቱ ፣ የእድሜ ጣሪያው ከፍ እንዲል ፣ እንደእዚኹም ፦ ለጤና ፣ ለትምሕርት ፣ ለመሠረተ ልማት ፣ ለቤት ፣ ለቴክኖሎጂ ፣ ወዘተ ያለው ቅርበት እንዲጨምር እና ኢትዮጵያዊው ከዓለም ስልጡን እና ዘመናዊ ሕዝብ አንዱ እንዲሆን ይፈልጋል።

ሆኖም እዚኽ መዋቅራዊ ሽግግር በማምጣት ከዓለም ስልጡን እና ዘመናዊ ሕዝብ መካከል የእሚያስመድበን ዕድገት ውስጥ የእሚያስገባን የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ላይ የእምንደርሰው በየትኛው ጎዳና ተጉዘን ነው የእሚለው ጉዳይ ፤ ቢያንስ ከ1966ቱ አብዮት አንስቶ እስከ ዛሬ ፤ 90% በላይ የሆነ ብሔራዊ መግባባት ከማግኘት ይልቅ ፤ ሐገር እንደ አከፋፈለ እና እንደ አለያየ ነው ያለው።

ልዩነቱንም በአንድ ዓረፍተ ነገር እናስቀምጠው ካልን ፤ ኢትዮጵያን ከስልጣኔው ማማ ላይ የእሚያወጣት ፤ ልማታዊነት ወይንስ ገበያ በእሚል በእሚል የእሚቀመጥ ነው።

ልማታዊነት ሲባል ፤ መንግሥት ከመደበኛ የመንግሥት አገልግሎት በማለፍ ፤ እንደ ነጋዴ የትርፍ ፍላጎት ሳይገዛው ፤ ወሳኝ በእሚባሉ ፦ እንደ ባንክ ፣ የኃይል አቅርቦት ፣ የውኃ አቅርቦት ፣ የቴሌኮም አገልግሎት ፣ ወዘተ ባሉ መስኮች በመሳተፍ ፤ ነጋዴው ትርፍ የለውም ብሎ የእሚተወውን ወይንም ለውስን የማሕበረሰብ ክፍል ብቻ የእሚያቀርበውን አገልግሎት ፤ ለሰፊው ሕዝብ ተደራሽ በሆኑ መልኩ በማቅረብ ነው ፤ ኢትዮጵያን ከዘመናዊነት ማማው ላይ ማውጣት የእሚቻለው ብሎ ማለት ነው።

ገበያ ነው ሲባል ደግሞ ፤ መንግሥት በዋናነት የሕግ ፣ የፖሊሲ እና የተቋማ ግንባታ ላይ በቀዳሚነት አተኩሮ ፤ የልማት ሥራም ሆነ ድጎማ ሲያደርግ ፤ ከግብር ገቢው አንጻር እንዲያደርግ ሲሆን እና እራሱን ከላይ ለመግለጽ ከተሞከረው ዓይነት የልማታዊነት አስተሳሰብ ሲገድብ ፤ ገበያው (የሐገር ውስጡም የዓለም ዓቀፉም) እራሱ ፤ ምንም እንኳን በትርፍ እሳቤ ቢዘወርም ፤ በሐገሪቱ ኹሉንም ዓይነት ምርት እና አገልግሎት በተወዳዳሪ ዋጋ እና ጥራት በማቅረብ ፤ ኢትዮጵያን ከስልጣኔው ማማ ላይ ያወጣታል ማለት ነው።

እንደ ገበያ መር የኢኮኖሚ መስመር ዕምነት ፤ ገበያ በትርፍ እሳቤ መመራቱ ፤ የልማታዊው አስተሳሰብ እንደ እሚለው ኢኮኖሚ ኢፍትኃዊ ስርጭት እና ብዝበዛ እንዲኖርበት ሳይሆን እሚያደረገው ፤ በውድድር ምክንያት ፦ ጥራት ያለው ምርት እና አገልግሎት በተወዳዳሪ ዋጋ ፤ በተሻለ ፍትኃዊ አሠረጫጨት ለሕብረተሰብ የእሚያዳርስ ነው የእሚሆነው።

እንደ እሚታወቀው ግን፦ በኢትዮጵያ ከ1966ቱ አብዮት አንስቶ እስከ ዛሬ የሐገሪቱ ማሕበረ ኢኮኖሚ የእሚመራው በልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብ ሆኗል።

ይኽ የፖሊሲ ምርጫ ፤ ምንም ዓይነት የማሕበረ ኢኮኖሚ ዕድገት በሐገሪቱ አላመጣም ማለት ባይቻልም ፤ ከእሚቻለው አንጻር ያስመዘገበው ውጤት ግን እምብዛም ነው።

ከ52 ዓመታት በኋላ ፦ ዛሬም በኢትዮጵያ ኋላ ቀር የሆነው ግብርና በኢኮኖሚው ዓመታዊ ምርት ላይ የ33% በመቶ ድርሻ ሲኖረው የኢንደስትሪው መጠን ደግሞ ከ4 እስከ 6% ነው። ያም ብቻ ሳይሆን ፤ በሐገሪቱ ለኢንደስትሪ ልማት የእሚያመቹ ምህዳር በአለመኖሩ ፤ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የብድር መረጃ ተመሥርተን ብናየው እንኳን መስኩ ከግብርና መስክ በላይ አክሳሪ ነው።

የሐገሪቱ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ52 ዓመታት የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችም በኋላ ፤ የዓለማችን ዝቅተኛ መደብ ውስጥ የእሚካተት የድኃ ሐገር ነው። በኢሕአዴግ ዘመን በ2025 ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ላይ እንደርሳለን ተብሎ የታለመ ቢሆንም ፤ አሁን 2026 ላይ ብንሆንም ግቡ አልተሳካም።

የሐገሪቱ የማክሮ ኢኮኖሚም ፦ በዋጋ ግሽበት ፣ በክፍተኛ የብድር ወለድ መጠን ፣ በክፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ፣ ከፍተኛ መጠን ባለው የሥራ አጥነት ፣ ወዘተ ችግሮች ተቀስፎ የተያዘ ነው።

በእዚያ ላይ ፦ በሐገሪቱ ያለው ፦ የቤት ፣ የትራንስፖርት ፣ የውኃ ፣ የትምሕርት ጥራት ፣ የጤና አገልግሎት ፣ ወዘተ ችግር ፤ ሐገሪቱን ከኋላ ቀር ሐገራት ጎራ የእሚያስመድባት ነው።

ሆኖም በእየገዜው የእሚቀያየረው የኢቶጵያ አመራር ፦ ፊውዳሊዝምን ሽሬ ጭሰኝነት አላስቀረኹም ፣ የአንደኛ ደረጃ የትምሕር ሽፋንን ከ90% በላይ አላደረስኩም ፣ ፒያሳን አፍርሼ ፓርክ በፓርክ አላደረግኹም ? ታዲያ እንዴት በሐገር ደረጃ ለውጥ አላመጣኽም ብላችኹ ትወቅሱኛላቹ የእሚል እንጂ ፤ ኢትዮጵያ ጀርመንን ወይንም እንግሊዝን መሆን ነበረባት ለምን አልሆነችም ብሎ የእሚጠይቅ መሆን አልቻለም።

ምክንያቱም ፦ በሐገርነት ታሪክ ብንኼድ ኢትዮጵያ ከጀርመን ወይንም ከእንግሊዝ ብትበልጥ እንጂ አታንስም። ታሪኩን ብንተወው ግን ፦ ኢትዮጵያ ጀርመንን እና እንግሊዝን እንደ አትሆን የእሚያግዳት ፦ የተፈጥሮ ኃብት እና የሰው ኃብት እጥረት ወይንም ሌላ ልዩ ምንም ምክንያት የለም ፤ እንደ ሐገር ይበጃል ብለን ከእምንከተላቸው የተሳሳቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በስተቀር።

ማንም ሊያረጋግጥ እንደ እሚችለው ፦ የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋሞቻቸውን በአግባቡ ከአደራጁ በኋላ ፡ ከኢትዮጵያ ያነሰ ወይንም ተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ የነበሩ ሐገራት በሙሉ ፤ ከ20 እስከ 40 ዓመት ባለ ግዜ ውስጥ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ካለ አንድ አንዴም ከባሰ የኋላ ቀር ኢኮኖሚ ደረጃ ተላቀው ወደ ኢንደስትራላይዝድ ሐገርነት ተቀይረዋል።

አሜሪካ ኢንደስትራላይዝ ያደረገቻው ፤ በወርቅ የተለበጠው በእሚባለው ከ1870 እስከ 1900 ባለው በ30 ዓመት ውስጥ ነው። ፖላንድ ከአሁኗ ኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ ከሆነ የኢኮኖሚ ቀውስ ወጥታ ዛሬ የነፍስ ወከፍ ገቢዋን ከ30 ሺ ዶላር በላይ ያደረሰቸው ከ1990 እስከ 2020 በአለው ግዜ ውስጥ ነው።

ደቡብ ኮሪያ በኃይለ ሥላሴ ዘመን ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ ካልሆነም ከኢትዮጵያ ያነሰ የስልጣኔ ደረጃ ላይ ከሆነችበት ወጥታ እዚኽ የደረሰችው ፤ ከ1970 እስከ 2000 በነበረው በ30 ዓመት ውስጥ ነው።

ብዙ ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ የማሕበረ ኢኮኖሚ ዕድገት የነበራት ጃፓን ፤ ያለ ምንም አብዮት ፊውዳልዝምን ተሻግራ ፤ የኢንደስትሪያላዝድ ዓለሙን የተቀላቀለችው ፤ ከ1873 እስከ 1910 በነበረው 40 ዓመታት ገደማ ነው።

የቺሊ ፣ የሲንጋፖር ፣ የታይዋን ፣ የቻይና ፣ ወዘተ ታሪክም ተመሳሳይ ነው።

የእየ ወቅቱ የኢትዮጵያ አመራር ግን ፤ ኢትዮጵያ መሆን የእምትችለው እና መሆን ሳትችል የቀረችው ሳይሆን የዕሚታየው ፤ ይልቁንም ፦ 1 ሺ ኪሎሜትር መንገድ አስገንብቻለኹ ፣ አዳዲስ 10 ፋብሪካዎች ከፍቻለኹ ፣ ወዘተ የእሚሉ ፤ ቁንጽል እመርታዎችን እያሳዩ ፤ ለሐገሬ ብለፋም ፤ ምስጋና ሳይሆን ትችት እየደረሰብኝ አመድ አፋሽ ሆንኩ ብሎ እሚያላዝን ነው የሆነው።

ከእዚኽ ዓይነቱ አላዛኝነትም ባሻገር ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የፖሊሲ ውይይት ባሕል አንጻር ፤ ትርጉም ያለው የፖሊሲ ውይይት አድርጎ ፤ ገበያ ከልማታዊነት ይሻላል ፤ ይሻላልም ብቻ ሳይሆን ፤ ብቸኛው ምርጫ ነው ብሎ ፤ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር ትንሽ ከብዷል ።

ለእዚኽ አንድ ትልቁ ምክንያት ደግሞ ፦ በኢትዮጵያ የፖሊሲ ውይይት ባሕል ፤ ውይይቱ በመረጃ እና በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ ፖሊሲዎችን በውጤታቸው የመመዘን ሳይሆን በርዕዮታዊ ወገንተኝነት ወይንም መሰል አካኼድ ፤ ሳይመራመሩ አቋም የመያዝ ነገር የእሚስተዋልበት መሆኑ ነው።

ሆኖም ፦ በባሕሪው ውስብስብ ወደ ሆነው የፖሊሲ የጽንሰ ኃሳብ ክርክር ውስጥ ሳንገባ ፤ የልማታዊ መንግሥት የእሚመራቸውን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በገበያ ከእሚመሩ እና ለትርፍ ከእሚሠሩ የንግድ ድርጅቶች ጋር ፦ በኢኮኖሚያዊ አፈጻጸማቸው በመመዘን ፤ እንደ ድርጅት በተናጠል ባላቸው ተወዳዳሪ አምራችነት እና የተናጠል ድርጅታዊ ተሳትፏቸው በሐገራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ሊጫወት ከእሚገባው እና እየተጫወተ ካለው ሚና አንጻር ብናነጻጽራቸው ፤ኢትዮጵያን ከዘመናዊነት ማማው ላይ ለማውጣት ፦ **<u>ልማታዊነት ወይንስ ገበያ</u>** ፤ የእሚለውን ምርጫ ቀላል ያደርገዋል ብዬ አስባለኹ።

ምክንያቱም ፦ ልማታዊነት ወይንም ገበያ የእሚለው መንገድ የተፈለገው ፤ ተቋማትን በተናጠል እና ሐገርን በወል በማሳደግ የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በመሆኑ ፤ በልማታዊ መንገድ የተመሩ ድርጅቶችን በገበያ ከተመሩ ድርጅቶች ፦

- በተናጠል ድርጅታዊ ትርፋማነታቸው እና ምርታማነታቸው እንደ እዚኹም
- የሐገርን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በማገዝ መጠን

ማወዳደር ከቻልን እና በኹለቱም መመዘኛ በገበያ የእሚመሩ ድርጅቶች በልማታዊነት ከእሚመሩት በላይ የተሻለ ውጤት ካስመዘገቡ ፤ ተቋሞቹ በገበያ እንዲመሩ ለመምረጥ ቀላል ይሆናል።

ለምሳሌ ፦ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤ በልማታዊ መንገድ ተመርቶ ፤ ከ100 ብር 20 ብር ማትረፍ ሲችል 10 ብቻ እያተረፈ ከሆነ እናበእዚያም ኺደት የሐገሪቱን ግማሽ ገበያ እንደ ተቆጣጠረ የገንዘብ ተቋምነቱ (As a financial institution that controls half of the national market) በሐገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውስጥ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ምርታማነነትን በ15 በመቶ ማሳደግ ሲኖርበት በ8 በመቶ ብቻ እሚያሳድግ ከሆነ ፥

በአንጻሩ ደግሞ የኢትዮጵያን ንግድ ከልማታዊነት ይልቅ በገበያ ሲመራ ፤ ባንኩ ትርፋማነቱ 10 በመቶ ከመሆን ይልቅ ወደ 20 በመቶ ቢያድግ እና በእዚኽም በእሚሰጠው ተወዳዳሪ እና ገበያ መር የባንክ አገልግሎት ምክንያት የሐገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በዓመት 8 በመቶ ከእሚሆን ይልቅ 15 በመቶ እንዲሆን ከአደረገው ፥

ለአንድ ኢትዮጵያዊ ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከልማታዊነት ይልቅ በገበያ ቢመራ ይሻላል ለማለት በጣም ይቀለዋል።

ምክንያቱም ፦ እንደ ሐገር የፈለግነው ፤ ተቋሞቻችንን በተናጠል እንደ ተቋም ፤ ሐገራዊ ኢኮኖሚውን ደግሞ በወል ፤ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ በማሳደግ ኢትዮጵያን ኢንደስትሪያላዝድ ከሆኑት ሐገራት ጎራ ማስገባት ከሆነ ፤ ምዘናችን መሆን ያለበት ፤ የእምንከተለው መንገድ ከግቡ አንጻር በእሚያስመዘግበው አፈጻጸም መሆን አለበት እንጂ እኛ የእምንወደው እና የእምንመርጠው መንገድ የቱ ነው በእሚል መሆን የለበትም።

በእዚኽ ፦ <u>**ልማታዊነት ወይንስ ገበያ**</u> በእሚለው ፕሮጀክትም ውስጥ ላደርግ የእምፈልገውም ፤ ንግድ ባንክን ጨምሮ የተወሰኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ልማታዊ ድርጅቶችን በማሳያነት በመውሰድ ፤ ተመሳሳይ ከሆኑ ከሌሎች በገበያ ከእሚመሩ ተቋማት ጋር በማነጻጸር ፤ እነ እዚክ የልማት ድርጅቶች በልማታዊ አስተሳሰብ በመመራታቸው ፦

1. በተናጠል እንደ ተቋም በገበያ ከእሚሰሩ ተመሳሳይ ተቋማት አንጻር ተወዳዳሪ ሆነዋል ?
2. በኢኮኖሚ ውስጥ ባላቸው ሚና አንድ በገበያ የእሚመራ ተመሳሳይ ተቋም ተመጣጣኝ ወይንም የተሻለ እገዛ አድርገዋል ?

በእሚል በመመዘን ፤ በተፎካካሪ መንገዶቹ ፦ በልማታዊነት እና በገበያ መካከል ያለውን ምርጫ ለማቅለል መሞከር ነው።

2 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፤ በማርች 2026 የኢትዮጵያ የገንዘብ ተቋማት ጫናን የመቋቋም ምዘና ሪፖርት (Financial Stability Report) ብሎ ባወጣው በእዚኽ ፦ FInancial-Stability-Report MARCH 2026 .pdf ሪፖርት መሠረት ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤ በኢትዮጵያ የባንክ ገበያ ውስጥ ያለውን ድርሻ እና ጥንካሬ እንዲኽ ብሎ አስቀምጦታል፦

- በሐገሪቱ ውስጥ ከእሚገኙት ባንኮች አንጻር 47.9 በመቶ የነበረው የንብረት ድርሻው ወደ 49.1 ከፍ ብሏል። ማለትም ፦ የንግድ ባንክ ንብረት በኢትዮጵያ ውስጥ ከእሚገኙት ከ25 በላይ የግልም የመንግሥትም ባንኮች ድምር ንብረት ጋር እኩል ነው።
- በሐገሪቱ ውስጥ በኹሉም ባንኮች ከተሰጡት ብድሮች አንጻር ፤ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተሰጠው ብድር ባለፈው ዓመት ከነበረበት 45.2 በመቶ ወደ 51.7 በመቶ አድጓል። ማለትም ፦ በሐገሪቱ ውስጥ በባንኮች ከተሰጡት ብድሮች በሙሉ ፤ ከግማሽ በላዩ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው የተሰጠው።
- በሐገሪቱ ውስጥ በኹሉም ባንኮች ተቀማጭ ከተደረጉት ገንዘቦች አንጻር ፤ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የነበረው ተቀማጭ ባለፈው ዓመት ከነበረበት 47.1 በመቶ ወደ 48.1 በመቶ አድጓል። ማለትም ፦ በሐገሪቱ ውስጥ ካለው ተቀማጭ ገንዘብ ወደ ግማሽ የእሚጠጋው ወይንም 48.1 በመቶው የተቀመጠው ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው።
- መንግሥት እና የልማት ድርጅቶች ፤ ከእሚሸጡት በንድ ውስጥ 43.1 የእሚሆነውን የእሚገዛው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው።

  "Accordingly, its market share in banking sector assets grew from 47.9 percent to 49.1 Similarly, its share in loans and bonds share went up from 45.2 percent to 51.7 percent, while its deposits market share increased from 47.1 percent to 48.1 percent, and capital market from 24.2 percent to 43.1 percent."

ይኽም ማለት ፦ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ከባንክ ጋር ተያይዘው የእሚደረጉትን የኢኮኖሚ ዕንቅስቃሴዎች ግማሹን ይቆጣጠራል ማለት ነው።

እንደገና ይኽም ማለት ፦ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፦ ብድር እና የውጭ ምንዛሪ በእሚያከፋፍልበት ግዜ ፤ ትርፋማ እና ምርታማ ለሆነ መስኮች በአግባቡ ካላከፋፈለ ፤ በብዙ ቢልየን የእሚቆጠር ገንዘብ ፤ ለትክክለኛው ነጋዴ በትክክለኛው ሰዓት ባለመድረስ ፤ የባንኩን ትርፋማነት ከመቀነስ ጋር አብሮ ፤ የሐገሪቱን ጠቅላላ ሐገራዊ ምርትም ሊቀንስ ይችላል።

ለምሳሌ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤ በ10% ወለድ የ100 ቢልዮን ብር የኢትዮጵያ መንግሥት ቦንድ ከአሚገዛ ይልቅ ፤ በ20% ወለድ ለአንድ ትርፋማ ነጋዴ ቢያበድረው ኖሮ ፤ የባንኩ ትርፍ በእጥፍ መጨመር ብቻ ሳይሆን ፤ የሐገሪቱ ጠቅላላ አገራዊ ምርት (ጠአም) ወይንም ጂዲፒ (GDP) ላይም ጭማሪ ሊያስከትል ይችላል።

አይደለም እንደ ኢትዮጵያ ባለ እና ንግድ ባንክ 50% የአሚሆነውን ገበያ ተቆጣጥሮ ፡-

- እስከ 80% የአሚሆነውን ብድሩን ለአትራፊ ሳይሆን ለፖሊሲ በአሚያበድርበት እና ብክነት በአሚፈጥርበት
- በእዚኽም የዋጋ ግሽበት በአሚያበዛበት
- 9.5 ቢልዮን ብር በዓመት በተበላሸ ብድር ምክንያት ከትርፉ በአሚቀንስበት ፤ ከጠቅላላ ብድሩ ወደ 56 ቢልየን ብር አሚበላሽ ብሎ ታሳቢ በአሚያደርግበት
- መክፈል ከአሚገባው ግብር ወደ 43% በሙቶ ተቀናሽ በአሚያገኝበት

ከኢትዮጵያ በጣም የተሻለ ነጻ ገበያ ባላቸው ብድር በበቂ ኹኔታ በአሚቀርብባቸው ኢኮኖሚዎች እንኳን ፤ ለምሳሌ ፡- በእዚኽ የአይ ኤም ኤፍ (IMF) Credit Expansion in Emerging Markets: Propeller of Growth?; by Mercedes Garcia-Escribano and Fei Han; IMF Working Paper No. 15/212; September 1, 2015 የጥናት ወረቀት መሠረት ፤ የኮንሲውመር (Consumer) የአሚባለው ብድር በ4% ሲጨምር የሐገሪቱ የጂዲፒ (GDP) ዕድገት በ0.3% እንደ አሚያድግ እና ለግል ኮርፖሬሽኖች የአሚሰጠው ብድር በ10% ሲያድግ የሐገሪቱ ጂዲፒ (GDP) በተመሳሳይ በ0.3% እንደ አሚያድግ ይተነበያል።

እንደ ጥናታዊ ጽሑፉ የኮርፖሬሽኖቹ የ0.3% የጂዲፒ (GDP) ዕድገት ለማምጣት 10% ዕድገት የፈለገበት ምክንያት ፤ ብድር ሲረክስላቸው ፤ ብሩን ወስደው ፤ መጠባበቂያ ገንዘብ አድርገው ስለ አሚያስቀምጡት ነው። ያ ካልሆነ እና እንደ እኛ ሐገር ብድር የተራበ ኮርፖሬሽን ባለበት ሐገር ፤ ምን አልባት በ4% የኮርፖሬት ብድር ዕድገት የኢኮኖሚውን ጂዲፒ (GDP) ዕድገት በ0.3 ማሳደግ ይቻል ይሆናል።

ይኽም ማለት ፡- በኢትዮጵያ ኹኔታ ፤ ንግድ ባንክ አሁን ለፖሊሲ የአሚያበድርበትን ኹኔታ ቢቀየር እና የአሚሰጠውን ብድር ከ50% እስከ 80% ለኮንሲውመር (Consumer) እና ለኮርፖሬት (Corporate) ማበደር ቢቻል ፤ በሐገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ቢያንስ ከ1.5% እስከ 6% የአሚደርስ ዓመታዊ የጂዲፕ (GDP) ዕድገት ጭማሪ ሊያስከትል ይችላል ማለት ነው።

ይኽ እንዲያው በጣም ኮንዘርቫቲቭ ግምት ነው ፤ የጂዲፒ ዕድገት ከእዚያም በላይ ሊሆን ይችላል።

ይኽም ማለት ፡-ለምሳሌ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በልማታዊ መንግሥት እሳቤ ከአሚመራ ይልቅ በገበያ የአሚመራ ቢሆን እና የአሚያበድርበት መርኽ ትርፋማነትን ታሳቢ ያደረገ ቢሆን ፤ ባንኩ የራሱን ትርፍ በእጥፍ ከማሳደግ ባለፈ ፤ ለምሳሌ፡- በአሚቀጥለው የበጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ 10% ያድጋል ተብሎ ከተገመተ ፤ ዕድገቱ ከ11.5% እስከ 16% ሊደርስ ይችላል ማለት ነው።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግን ከገበያ ይልቅ በልማታዊ መንግሥት መርኽ ስለ እሚመራ ፤ በእዚኽ መልኩ የራሱን ትርፋማነት ከመጨመር እና የሐገሪቱን ዓመታዊ ዕድገት አሁን ከእሚያድግበት በላይ ከማሳደግ ይልቅ ፤ የእሚከተሉትን ዘርፈ ብዙ ጉድለቶች በማሳየት ደካማ ባንክ ከመሆን ባሻገር የሐገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እያዘገየ ነው።

2.1 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ላይ የእሚቀርብ "ክስ"

በአንድ ጤናማ ኢኮኖሚ ውስጥ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያሉ የገንዘብ ተቋማት ፤ የአንድ ሐገር ልማት የደም መዘዋወሪያ በመሆን ፤ ገንዘብን በፍጥነትን ወደ ትርፋማ ምርት እና አገልግሎት ለእሚለውጡ የንግድ መስኮች በማቅረብ ፤ የሐገርን መዋቅራዊ ሽግግር ያግዛሉ።

በእዚኽም መሠረት ፦ የባንኮች ዋና አገልግሎት በጣም ውስን የሆነውን የዜጎች ቁጠባ ቀጣይነት ወደ አለው የኢኮኖሚ ዕድገት መቀየር ነው።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግን ከትርፋማነት ይልቅ በልማታዊነት ስለ እሚመራ ፤ ይኽን ታሪካዊ እና ሐገራዊ አደራውን በአግባቡ ሊወጣ አልቻለም።

ምክንያቱም፦ ባንኩ ገንዘብ የእሚያበድርበት መርኽ ፤ ትርፋማ እና ዝቅተኛ ስጋት ያለባቸው መስክ በመምረጥ ፤ የእራሱን የስጋት መጠን ቀንሶ ትርፉን በእሚያበዛበት ሳይሆን የፖሊሲ ግቦችን ማሳካት በእሚል ፤ ትርፋማ ይኹኑ አይሁኑ ፤ በፖሊሲ ቅድሚያ ለተሰጣቸው መስኮች የእሚያበድር በመሆኑ ፤ የእራሱንም የሐገሪቱንም ዕድገት ላይ የተቀመጠ ማነቆ ሆኗል።

በእዚኽ አካኼዱ ፤ ንግድ ባንክ ፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዝቅተኛ ገቢ (Ethiopia's economic status of low income economy) የክቡር ዘብ ሆኗል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፦ ከትርፋማነት ይልቅ የዕድል ዋጋን የእሚያበዛ (Immense opportunity cost) ፤ የኋላ ቀርነት ዘብ መሆኑን የእሚያጋልጡ ችግሮችን ፤ ከእራሱ የ2023/24 ዓመት ሪፖርት ላይ በመመርኮዝ ማስረጃዎችን እናቅርብ፦

2.1.1 ከገበያው አንጻር ዝቅተኛ ወለድ ለእሚከፍሉ መስኮች ከፍተኛ ብድር ይሰጣል

የእሚቀርብበት ክስ: በተቀናጀ እና በመንግሥት ትዕዛዝ ስለ እሚያበድር ኃብት ለእሚያባክኑ መስኮች ከፍተኛ ብድር ይሰጣል

- **የመንግሥት ቦንድ:** 64.5% የእሚሆነው የባንኩ ብድር ዝቅተኛ የወለድ መጠን ለእሚከፍሉ የመንግሥት እና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ቦንድ ግዢ የዋለ ነው።
- **የልማት ድርጅቶች ብድር:** ከመንግሥት እና ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቦንድ የእሚተርፈው አብዛኛው የባንኩ የቁጠባ ገንዘብም ፤ ዝቅተኛ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ላላቸው ፤ በመንግሥት ፖሊሲ ለተመረጡ መስኮች በብድርነት የእሚሰጥ ነው።
  - **ለምሳሌ ፦** 70% የእሚሆነውን ብድር የእሚሰጠው ፤ ከ9.46% እስከ 21.9% የእሚደርስ ያለመከፈል ዕድል ላላቸው ለፋብሪካ ፣ ለግንባታ እና ለውጭ ንግድ ነው የእሚሰጠው።
  - **በራሱ በባንኩ የ2023/2024 መረጃ መሠረት መስኮቹ የእሚከተለው የአለመከፈል አደጋ ያላቸው ናቸው፦**
    - ማኑፋክቸሪንግ (9.46% risk)
    - ሕንጻ እና ግንባታ (17.3% risk)
    - ዓለም ዓቀፍ ንግድ (21.9% risk)
- ይኸም ማለት ባንኩ ለማንፋክቸሪንግ ከእሚያበድረው 100 ብር 10 ብሩ ያለመከፈል ዕድሉ ከፍተኛ ነው ፣ ለሕንጻ እና ለግንባታ ከእሚያበድረው 100 ብር 17 ብሩ ያለመከፈል ዕድሉ ከፍተኛ ነው ፣ ለዓለም ዓቀፍ ንግድ ከእሚያበድረው 100 ብር 22 ብሩ ያለመከፈል ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ይኽን በ2024 ዓም የደቡብ አፍሪካው ስትንዳርድ ባንክ ኮርፖሬት እና ኢንቨስትመንት ባንኪንግ (Corporate and Investment Banking) በእሚባለው መስክ ላበደረው ወደ 1 ትሪልየን ራንድ የእሚጠጋ ብድር የእማይከፈል ብሎ በስጋትነት ካስቀመጠው 3 ቢልየን ራንድ ጋር ብናነጻጽረው ፤ የስታንዳርድ ባንክ የብድር የስጋት መጠኑ 0.29% ብቻ ሲሆን የኢትዮጵያው ንግድ ባንክ ግን በአማካኝ ከ15% በላይ ሆኖ እናገኘዋለን።
- **ድምዳሜው:** ባንኩ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ሲመዘን ፤ የገበያን ምልክት ሳይሆን ፤ የመንግሥትን የፖሊሲ ትዕዛዝ ስለ እሚከተል ፤ ሌሎች ባንኮች ከእሚያደርጉት በላይ ፤ ከፍተኛ ኪሳራ ያደርሱብኛል ብሎ ለእሚፈራቸው መስኮች ፤ ከፍተኛ ብድር በመስጠት ፤ የሐገር ኃብት ያባክናል ፣ የአዳጊ መስኮች ዕድል ይዘጋል ፣ ዋጋ ያዛባል ፣ ወዘተ።

2.1.2 ሰፊ መጠን ያለውን የሐገሪቱን የቁጠባ ገንዘብ ከእላይ በተጠቀሰው መንገድ እማያዋጡ መስኮች በስፋት (በሙላት) ያበድራል

የእሚቀርብበት ክስ: የፖለቲካ ሽፋንን ተተጥቅሞ ፤ ማግኘት የእማይገባውን ርካሽ ገንዘብ እያገኘ መልሶ በእማይሆን መንገድ ስለ እሚያበድረው ባንኩ ኪራይ ሰብሳቢ ሆኗል ፤ ።

- **ርካሽ የወለድ መጠን የመሰብሰብ ኪራይ ሰብሳቢነት:** የመንግሥት ደሞዝ ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የገንዘብ እንቅስቃሴ እንዲኹም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በዋናነት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ስለ እሚጠቀሙ ወይንም የመጠቀም ግዴታ ስለ አለባቸው ፤ ባንኩ ምንም ወለድ የሌለው ወይንም ዝቅተኛ የወለድ መጠን ያለው ከፍተኛ ገንዘብ ያገኛል። ይኽም ዓይነተኛ የክራይ ሰብሳቢ ድርጅት ባሕሪ ነው ፤ ባንኩ የእሚያገኘውን ርካሽ የቁጠባ ገንዘብ የእሚያገኘው በተወዳዳሪነት ሳይሆን ተወዳዳሪነት በእማያበረታታ የመንግሥት ውሳኔ እና አሠራር ምክንያት በመሆኑ።
- **ትልቅ የእሚመስለው የባንኩ ትርፋማነት ብዥታ:** በባንኩ ዓመታዊ ሪፖርት ላይ የእሚቀርበው ከንብረት እና ከካፒታል አንጻር ከፍተኛ የተባለ ትርፋማነት (ROA and ROE) ፤ ዕውነትም ባንኩ ትርፋማ ሆኖ ያመጣው ሳይሆን ፤ በመንግሥት ፖሊሲ እና በሐገሪቷ ኹኔታ አማካኝነት ፤ አግቶ የያዘውን ርካሽ የቁጠባ ገንዘብ ፤ ምንም ተወዳዳሪነት በሌለበት መንገድ ፤ ለመንግሥት እና ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ፤ በፖሊሲ ትዕዛዝ በማበደር ነው።
- **የግሉን መስክ ማቀንጨር:** ባንኩ የሐገሪቱን ግማሽ የብድር አገልግሎት ስለ እሚቆጣጠር እና ያለውን የማበደር አቅም 80 ከመቶ በላይ የእሚሆነውን ለትርፋማነት ሳይሆን ለመንግሥት በርካሽ ስለ እሚያበድር ፤ በሐገሪቱ የግሉ መስክ በቂ ብድር በማጣት ቀንጭሮ እንዲቀር አድርጓል።

2.1.3 የውሸት የተበላሸ ብድር መጠን ስሌት

ክስ: በመደበኛው የባንክ አሠራር አንድ ብድር ከ90 ቀናት በላይ ክፍያ ሲያዘገይ እንደ ተበላሸ ብድር መታየት የእሚጀምርበትን አሠራር ለማለፍ ፤ ባንኩ ለመንግሥት የእሚያበድራቸው ብድሮች ፤ መክፈል አቅቷቸው የክፍያ ግዜያቸውን ሲያልፉ ፤ የተበላሹ ብድሮች ብሎ ብድሮቹን ከማስቀመጥ ይልቅ ፤ የክፍያ ወቅታቸውን በመለወጥ እና መሰል ስልቶችን በመጠቀም ብድሮቹ ጤናማ እንደ ሆኑ ያሳያል።

- **የንብረትን አሰያየም መቀየር:** ከፍተኛ መጠን ያላቸው ለመንግሥት የልማት ድርጅት የተሰጡ ብድሮች ሲከስሩ እና መክፈል ሲያቅታቸው ፤ የተበላሸ ብድር ከእሚባሉ ይልቅ ፤ ወደ መንግሥት ቦንድነት ተቀይረዋል።
- **የውሸት የተበላሸ ብድር መጠን:** ከእዚኽ የተነሳ ባንኩ ካበደርኩት ብድር የተበላሸብኝ 3.64% ብቻ ነው የእሚለው ፤ ትልልቆቹን የተበላሹ ብድሮች የመንግሥት ቦንድ ውስጥ ከደበቃቸው በኋላ ያሉትን ብቻ እየቆጠረ ነው።

2.1.4 የካፒታል መቃብር ስፍራ ነው (የእሚያበድራቸው ብድሮች የመክሰር ዕድላቸው ከፍተኛ ነው)

የእሚቀርብበት ክስ: ኃብት ያወድማል

- **ቀላል የእማይባል ትርፉን ለተበላሸ ብድር መሸፈኛ ያደርጋል:** በ2023/2024 የበጀት ዓመት በተበላሸ ብድር ምክንያት ያጣው ገቢ 9.51 ቢልዮን ብር ሲሆን ፤ ይኽም ከግብር በፊት የነበረው

የባንኩ ትርፍ 35% ሲሆን ከግብር በኋላ ያለው የባንኩ ትርፍ ደግሞ 43.19% ነው።ባንኩ በእዚያ ዓመት በተበላሸ ብድር ምክንያት ያጣው የ9.51 ትርፍ የእዚያን ዓመት የአቢስንያ ባንክ ከግብር በኋላ ያተረፈው የተጣራ ትርፍ **4,237,996,000** ኹለት እጥፍ ነው። በእዚኽ መመዘኛ በእዚያው የበጀት ዓመት አብሲንያ ባንክ ለተበላሸ ብድር የከፈለውን ክፍያ ከተጣራ እና ከአልተጣራ (ከግብር በኋል እና ከግብር በፊት) ትርፉ አንጻር ስንመዝነው 27.57% እና 22.13% በመቶ ሆኖ ነው የእምናገኘው። ስለ እዚኽ፦ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤ ከሐገር ውስጡ ከአብሲንያ ባንክ ጋር እንኳን ኃብት በማባከን ቢወዳደር ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የበለጠ አባካኝ ሆኖ ነው እሚገኘው።

- **መንግሥት እንኳን አስተማማኝ ተበዳሪ ያልሆነበት:** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቦንድ እና በግምጃ ቤት ሰነድ በመሳሰሉ መንገዶች ለመንግሥት ካበደረው 785,298,333,929 ውስጥ 20,670,348,017 ሊከፈለኝ የእማይችል ብሎ የያዘው ነው። ይኽም በፐርሰንት ሲቀመጥ 2.6% ነው። ይኽም ከባንኩ ችግር በአሻገር መንግሥት ራሱ ጥሩ ተበዳሪ እንደ አልሆነ እሚያሳይ ነው። እሚገርመው በባንኩ መረጃ መሠረት ኮንሲውመር (Consumer) እና ሙራባኃ የእሚባሉት የብድር ዓይነቶች ከመንግሥት የተሻለ ጥሩ ተበዳሪ ሆነው ፤ የክስረት መጠናቸው የኮንሲውመሩ 0.5% ሲሆን የሙራባኃው 1.9% ነው። የመንግሥት የተበዳሪነት ደረጃ በፖሊሲ እንኳን ታስሮ ከግብርናው መስክ ጋር የእሚነጻጸር ነው ፤ ምክንያቱም በባንኩ መረጃ መሠረት ለግብርና የተሰጠ ብድር የመበላሸት እድሉ 3.9% በመሆኑ። በአንጻሩ ባንኩ ለኮንሲውመር (Consumer) የእሚያበድረው ብድር ያለው አዋጭነት በሌሎች በሰለጠኑ ሐገራት ከመንግሥት በንድ ጋር የእሚነጻጸር አደጋ ነው ያለው ፤ ምክንያቱም ፦በአሜርካ ፣ በእንግሊዝ ፣ በጃፓን ፣ ወዘተ ለመንግሥት የተሰጠ ብድር የመበላሸቱ እድል ከ0 – 0.5% ድረስ ብቻ ነው ተብሎ ነው የእሚዘገበው።
- **የክስረት መጠን:** ባንኩ ፤ በእየ ብድር ዓይነቶቹ ፤ በጠቅላላ ሊበላሹ ይችላሉ ብሎ የያዘው ግምት ወደ 56.5 ቢልየን ብር ሲሆን ፤ ይኽም የባንኩ የኹለት ዓመት ተኩል የተጣራ ትርፍ መጠን ነው።

2.1.5 የገበያ ሳይሆን የፖሊሲ ብድር ያስከተለው ኪሳራ

የእሚቀርብበት ክስ: ባንኩ የመንግሥትን ፖሊሲ ፋይናንስ ማድረጊያ ተቋም እንጂ እንደ ስሙ ንግድ ባንክ አይደለም

- **ንግድን ታሳቢ ያልተደረጉ ብድሮች:** ባንኩ እንደ ማኒፋክቸሪንግ እና ኮንስትራክሽን ላሉ መስኮች የእሚያበድረው መንግሥት መስኩን ለማበረታታ ካለው ፍላጎት ፤ ስለ እዚኽ በፖሊሲ ትዕዛዝ ነው እንጂ ፤ የማኒፋክቸሪንጉ እና የኮንስትራክሽን መስኩ ፤ በቂ ምዘና ተደርጎበት ምን ያኽል የገንዘብ ፍሰት መፍጠር ይችላል (rigor of cash-flow analysis) ፣ ብድሩን የእሚወስዱት ተቋማት በመስኩ የተመሰከረ ብቃት አላቸው (technical merit) ፣ ወዘተ በእሚል ተመዝነው አይደለም። አኹን ባለው ተጨባጭ ኹኔታ ፤ እንደ እኔ ሙራባህ የእሚባለው አከራካሪ ስለ ሆነ እናውጣውና ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ አዋጭ የብድር መስኮች ኮንሲውመር (Consumer Loan) እና ግብርና ናቸው። እሚገርመው ባንኩ የፖሊሲ ባንክ ቢሆንም እና መረጃ ላይ ትኩረት ባይሰጥም ፤ የእራሱ የብድር መረጃ የእሚነግረን ነገር

፤ ማለትም ፡- በአኹኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ውስጥ አዋጭ የብድር መስክ ኮንሲውመር (Consumer) እና ግብርና መሆኑ ፤ የኢኮኖሚው ሳይንስ ኢትዮጵያ የዕድገት ኮሪደሯ ግብርናን ማዘመን እና የሕዝቡን የፍጆታ አቅም ማሳደግ ነው የእሚለውን መርኽ በጣም የእሚደግፍ ሆኖ ነው ያገኘኹት። በሌላ አነጋገር ፤ መንግሥት ልማታዊነት ብሎ ባንኩን ቢያስረውም ፤ የባንኩ የራሱ የብድር መረጃ ፤ ገበያ ነው እኔንም ትርፋማ የእሚያደርገኝ ፤ የሐገሪቱንም ዕድገት እሳት አንድዶ ሳይሆን አምፖል አብርቶ የእሚያድር የእሚያደርገው እያለ ነው።

- **የልማታዊነት መንገድ ውድቀት:** ኢትዮጵያ ይኽን መሰል ፤ ኢንደስትራላይዜሽንን ከታች ወደ ላይ በማደግ ሳይሆን በመንግሥት ድጎማ እና ትዕዛዝ ከዕላይ ወደ ታች ለማምጣት የኼደችበት መንገድ ፤ ሐገሪቱን ዛሬም በዋናነት የኋላ ቀር ግብርና ሐገር እና ኢንደስትሪው ከ52 ዓመት መንግሥታዊ እንክብካቤ በኋላ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ከ4 -6% ገደማ እንዲሆን ያደረገ ነው ፤ የግብርናው ከ33% በላይ ሲሆን። ይኽም የልማታዊው መንገድ በኢትዮጵያ እንደ ነጠፈ ያሳያል።

2.1.6 ስኬትን የማጋነን አባዜ

የእሚቀርብበት ክስ: የተጋነነ የሥራ ማስኬጃ ወጪ

- **የማጋነን ጭምብል:** ባንኩ ካለው ንብረት አንጻር ትርፉን በእሚለካው (ROA – Return on Asset) የእሚባለውን መለኪያ ሲጠቀም ፤ ምንም እንኳን መለኪያው የተጣራ ትርፉን እንዲጠቀም ቢሆንም የእሚለው ፤ ባንኩ ግን ግብር ሳይከፍል በፊት ያለውን ትርፉን ይጠቀማል ፤ ኃሳቡም ከንብረቴ አንጻር በጣም ከፍተኛ አትርፈያለኹ ለማለት ነው። ያም ብቻ ሳይሆን ፤ ከንብረት አንጻር ትርፌ (ROA – Return on Asset) 1.9% ገደማ ነው ሲል ፤ ይኽ ቁጥር ባንኩ ከግብር በፊት ያለውን ትርፉን ተጠቅሞ ከእሚያመጣው በላይም ነው። በአጭሩ ከግብር በፊት ያለ ትርፍ ብቻ ሳይሆን የእሚጠቀመው ቁጥሩን ከ1.5 ወደ 1.9 ከፍ አድርጎ ይዘግባል። ይኽ ቁጥር ደግሞ በዓለም ላይ አሉ እሚባሉት ባንኮች ጋር ሲወዳደር እንኳን ከፍተኛ ነው ፤ ለምሳሌ፡- ሲቲግሩፕ እበ2024 ንብረ ከትርፌ አንጻር (ROA) 0.48% ገደማ ነው ብሎ ነው ሪፖርት ያደረገው ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደግሞ ከአንተ 4 እጥፍ ነኝ እያለ ነው።

- **መመዘኛ ማሳከር:** ይኽን መሰል ትርፋማነት ያለው እና እንደ ሲቲግፕ (Citigroup) ያሉ የዓለማችንን ግዙፍ ባንኮች ራሱ አስከነዳለኹ የእሚለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግን ፤ ከሠራተኛ አንጻር ትርፋማነቱ እና ኃብቱ ሲመዘን (Profit per employee, Profit per asset) አይደለም እንደ ሲቲግሩፕ ካሉት ዓለም ዓቀፍ ባንኮች እንደ ስታንዳርድ ባንክ ካሉት አፍሪካዊ ባንኮች አንጻር እንኳን በብዙ እጥፍ ያንሳል። ለንጽጽር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን እና የደቡብ አፍሪካውን ስታንዳርድ ባንክን እናስተያይ፦

ባንክ	ንብረት በሠራተኛ	በዶላር	ትርፍ በሠራተኛ	በዶላር ሲገለጽ
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ	**17,516,467.43 (ብር)**	**በ57 ብር ታስቦ ፤ 307, 306.44**	**277,579.76 (ብር)**	**በ57 ብር ታስቦ ፤ 4,869.80**
ስታንዳርድ ባንክ (ደቡብ አፍሪካ)	**71,700,000.00 (ራንድ)**	**በ16 ራንድ ታስቦ ፡ 4,481,250**	**973, 220 (ራንድ)**	**በ16 ራንድ ታስቦ ፤ 60, 826.25**

ማለትም ፡- የሠራተኛ ምርታመነትን ለማሳደግ ቴክኖሎጂ ከመጠቅምም አንጻር ሆነ በሠራተኛ ደረጃ ትርፋማ በመሆን ሲመዘን ፤ የደቡብ አፍሪካው ስታንዳርድ ባንክ ከኢትዮጵያው ንግድ ባንክ አንጻር ከ12 እጥፍ በላይ ምርታማ ሆኖ ነው የእሚገኘው። በምርታማነት መመዘኛ በእዚኽ መልኩ ኋላ የእሚቀረው ንግድ ባንክ ግን እንደ ከንብረት አንጻር ትርፉ (ROA) ባሉት የትርፋማነት መመዘኛ ሲመዘን አይደለም ከስታንዳርድ ባንክ ከሲቲግሩፕ እበልጣለኹ የእሚል ነው። ለእዚኽ መጣረስ ምክንያቱ ደግሞ ፡- ባንኩ ተወዳዳሪ ሳይሆን ኪራይ ሰብሳቢ በመሆኑ ፤ ርካሽ የቁጠባ ገንዘብ በከፍተኛ ደረጃ ለመንግሥት በማበደር ስለ እሚሠራ ፤ ትርፉ የእሚመጣው በሠራተኛው ምርታማነት ሳይሆን ፤ ባንኩ ሞኖፖሊ የተሰጠው ኪራይ ሰብሳቢ በመሆኑ ነው።

2.1.7 የግብር ድጎማ ይቀበላል

የእሚቀርብበት ክስ: ባንኩ ከፍተኛ የትርፍ መጠን እንዲያስመዘግብ ካደረጉት ነገራቶች አንዱ ፤ ለምሳሌ ፡- በ2023/2024 የበጀት ዓመት ፤ ከትርፉ ላይ መክፈል ከነበረበት ግብር ወደ 43% ገደማውን አልከፈለም ፤ ምክንያቱም ፡- ከመንግሥት ቦንድ ግዢ ላይ የእሚገኝ ትርፍ ግብር ስለ እማይከፈልበት።

- **4 ቢልየን ብር የግብር እፎይታ ነበረው:** ምንም እንኳን የሐገሪቱ ሕግ ባንኩ ከትርፉ ላይ 30% ግብር መክፈል አለበት ቢልም ንግድ ባንክ የከፈለው 17% ብቻ ነበር ፤ ምክንያቱም ከመንግሥት ቦንድ የእሚገኝ ትርፍ ግብር ስለ እማይከፈልበት እና ባንኩ ደግሞ በጠቅላላ ካበደረው ብድር 65% ያበደረው ለመንግሥት በበንድ ግዢ በመሆኑ።
- **ከቦንድ የእሚገኝ ገቢ ግብር እንደ አይከፈልበት ማድረግ:** ጤናማ የሚባሉ ሐገራት ከቦንድ ግዢ የእሚገኝ ገቢን እንደ ሌላ እንደ ማንኛውም ገቢ ግብር ይሰበስቡበታል። በእኛ ሐገር ግን ፡-

1. የመንግሥትን ቦንድ በአብዛኛው የሚገዛው ንግድ ባንክ ስለ ሆነ እና ንግድ ባንክም የመንግሥት ስለ ሆነ ፤
2. የኢትዮጵያ መንግሥት እጅግ ብኩን እና ሰነፍ ተበዳሪ በመሆኑ ፤ ገበያው በሚገባ አምኖት ገንዘብ ስለ ማያበድረው ፤

   የሐገራችን የልማታዊነት አስተሳሰብ ፤ የመንግሥትን የበጀት አስተዳደር አስተካክሎ እና ሌላውን የኢኮኖሚ ክፍል አስተካክሎ ፤ ከገበያው በርካሽ ብድር የሚያገኝበትን እና ከተበደረው ብድር ላይ ከሚገኘው ገቢ ላይ ተገቢውን ግብር ከመሰብሰብ ይልቅ ፤ እጅግ ኢምክንያታዊ በሆነ መንገድ ፤ ከእራሱ ባንክ ገንዘብ ያለ ገበያ መርኽ በርካሽ እየተበደረ ፦

   - ተወዳዳሪነቱ እና አምራችነቱ በገበያ ባልተመሠከረለት መስክ ላይ በርካሽ ያገኘውን ብድር እየበተነ የዋጋ ግሽበት ይፈጥራል
   - የዋጋ ግሽበቱ የገንዘብ ወለድ መጠንን ያስወድዳል
   - የግሉ መስክ በቂ ብድር እንደ አያገኝ ያደርጋል ፤ በእዚያም ኢኮኖሚ ያቀዛቅዛል
   - በርካሽ ያገዛኝን ባንክ አግዛለኹ በሚል የቂል ኢኮኖሚክስ ከቦንድ የሚገኝ ገቢ ግብር አይከፍልም በማለት ሐገሪቱን በአንድ ዓመት ብቻ እስከ 4 ቢልዮን ብር የግብር ገቢ ያሳጣል
   - ባንኩን ከትርፋማነቱ በላይ ትርፋማ አድርጎ በማቅረብ ፤ የባንኩን ዝቃጭነት ይደብቃል

- **የሕዝበኝነት የትምክህት አባዜ:** በኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያን በመሳሰሉ ኋላ ቀር ሐገራት ፤ የልማታዊነት አስተሳሰብ ፤ በተሳከረ የኢኮኖሚ ሳይንስ ግንዛቤ ፤ እንዲኽ አድርጎ እራሱን ፦ የጸረ ምርታማነት ፣ የኢኮኖሚ ውሸት እና የስረዓታዊ ሙስና ክቡር ዘበኛ አድርጎ ፤ ሐገራችንን በድህነት አዙሪት ውስጥ አቆይቷል።

2.1.8 ብቃት ያለው የካፒታል አደላደል አለኝ የሚል ቅዠት (THE CAPITAL ADEQUACY FICTION)

የሚቀርብበት ክስ: የካፒታል ድልድል ስጋት ደረጃ አመዛዘን ክፍተትን በመጠቀም እና በማዛባት ጠንካራ አቋም (financial strength) እንደ አለው ለማስመሰል ይሞክራል።

- **በመስኩ ቋንቋ የካፒታል አደላደል ብቃት ወይንም CAPITAL ADEQUACY RATIO (CAR)፡** የሚለካው ከባንኩ ካፒታል አንጻር ባንኩ ያበደራቸው የትኞቹ ብድሮች የመክሸፍ አደጋ አለባቸው ብሎ የሚመዝን ነው።
  - የሚለካበትም መንገድ የባንኩን ካፒታል ሪስክ ላለበት ብድር መጠን በማካፋል ነው (CAR= Capital/Risk Weighted Asset)።

- ሪስክ ያለበት ብድር አሰላል መርኹም ለምሳሌ ፡- በአብዛኛው ሐገር የመንግሥት ቦንድ እና የግምጃ ቤት ሰንዶች በጣም አስተማማኝ ስለ ሆኑ ዜሮ ሪስክ እንደ አለባቸው ተደርገው ይወሰዳሉ ፤ የኮርፖሬሽኖች የተበደሩ ብድሮች መቶ በመቶ ሪስክ እንደ አላቸው ተደርገው ይወሰዳሉ ፤ ለሌሎች ባንኮች የተበደሩ ብድሮች ከ20 እስከ 50 በመቶ ሪስክ ያላቸው ብድሮች ተብለው ይወሰዳሉ።

- **የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ** ፡ 65% በመቶ የእሚሆነውን ብድሩን ፤ በ7ኛው ክስ በተገለጸው መሠረት በተንጋደደ መልኩ ለመንግሥት በቦንድ እና በግምጃ ቤት ሰነድነት ስለ እሚያብድር እና የቀሩትን እና ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች የእሚያበድራቸውን ብድሮች ደግሞ በእዚኹ በገበያ ብድር ማግኘት በእማይችለው መንግሥት ዋስትና ወይንም ጋራንቲ የእሚያበድር በመሆኑ ፤ ምንም እንኳን ከዓለም ዓቀፍ መመዘኛ አኳያ በጣም ሪስክ ያለበት አበዳሪ ቢሆንም ፤ ካበደርኩት 1,073,046,300,000 ውስጥ ሪስክ ያለበት የብድር መጠን 300, 260, 011, 378 ብቻ በመሆኑ እና የካፒታል መጠኔ ደግሞ 87, 926, 746, 539 በመሆኑ ፤ የካፒታል አዲኩዌሲዬ (CAR) 29.57% ፤ በማለት ዝቅተኛ የሪስክ መጠን እንደ አለበት ያስመስላል። ዕውነታው ግን ስጋት ያለበትን ተበዳሪውን ለተበደረው ብድር ዋስ ወይንም ጋራንተር በማድረግ ነው የባንኩን የስጋት መጠን የእሚቀንሰው። እስኪ አስቡት ፤ ለሰው ቢልዮኖች አበድራቹ ፤ እራሱ ተበዳሪውን ላበደራችሁት ብድር ዋስ ካደረጋችሁት በኋላ ፤ ያበደረኩት ብድር ዝቅተኛ ስጋት ነው ያለበት ምክንቱም ተበዳሪው ዋስ አለው ብትሉ። የኢትዮጵያ ልማታዊያን ቀልድ ላይ ናቸው።

- **ከስታንዳርድ ባንክ ሲነጻጸር:** ምንም እንኳን የደቡብ አፍሪካው ስታንዳርድ ባንክ ያስተናገደው ዓመታዊ የብድር ብልሽት ስጋት መጠን (0.29%) ቢሆንም እና የኢትዮጵያን ንግድ ባንክ የብድር ብልሽት ስጋት መጠን ወደ 15% ቢሆንም ፤ የኢትዮጵያው ንግድ ባንክ ግን የአድኩዌሲ ሬቱ (Capital Adequacy Ratio) ከስታንዳርድ ባንክ ከእጥፍ በላይ ነው። ምክንያቱም ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አድኪዌሲ ሪፖርት ሲደረገ 29.57 ሲሆን የስታንዳርድ ባንክ ግን 13% ገደማ ነው። በሌላ አማርኛ ፡- ንግድ ባንክ ፡- ብድር የማበላሸት ዕድሌ ከስታንዳርድ ባንክ ቢበልጥም ያለብኝ የተበላሸ ብድር ስጋት ግን ከስታንዳድ ባንክ ከ30 እጥፍ በላይ ያነሰ ነው እያለ ነው። የእዚኽ ሚስጥሩ ደግሞ ግልጽ ነው ፡-
  - **አንድ ብድር ሲበላሽበት ወደ መንግሥት ቦንድ በመቀየር ሲሆን**
  - **ኹለተኛ ደግሞ እማያስተማምኑ ለመንግሥት የተሰጡ ብድሮችን በእራሱ በእማያስተማምነው ተበዳሪው መንግሥት ዋስትና ፤ የስጋት መጠናቸውን በመቀነስ ነው**

- **የወረቀት ላይ አስተማማኝ:** ከእዚኽም የተነሳ ባንኩ የወረቀት ላይ ነበር ነው። ምክንያቱም ፡- ይኽ ከፍተኛ ሪስክ የመቋቋም ቁጥር የመጣው ከባንኩ የካፒታል አደላደል ጥንካሬ ሳይሆን ፤ ባንኩ በጣም ስጋት ያለባቸውን ብድሮች ወስዶ በመንግሥት ስም እና በመንግሥት ዋስትና ፤ ስጋት ወይንም ሪስክ አልባ በእሚያደርግ የአካውንቲንግ ጫወታ የሪስክ ወይንም የስጋት መጠናቸውን ስለ እሚቅየር ነው። መንግሥታዊ ኪራይ ሰብሳቢነት እና ስንፍና ይለዋል ይኽ ነው።

2.1.9 ሞኖፖሊ

የእሚቀርብበት ክስ: በሐገሪቱ ውስጥ የገንዘብ ተቋማት በመወዳደር ብድር በርካሽ እንደ አያቀርቡ በር ዘግቷል

- **የግሉን መስክ ማድከም:** ንግድ ባንክ የሐገሪቱ ባንኮች ተደምረው ያላቸውን ካፒታል እና የሐገሪቱን ቀጠባም ግማሹን በመያዝ ፦ የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ ፣ የወለደ ዋጋ ፣ ወዘተ በመወሰን ከእርሱ ይልቅ ተወዳዳሪ የሆኑ ሌሎቹን ባንኮች ከውድድር ውጭ ያደርጋል።
- **ፈጠራን ማዳከም:** ባንኩ በመንግሥት ፖሊሲ እና አሠራር ምክንያት በውድድር ከእርሱ የእማይወሰድ እንደ ርስት የተሰጠው ቁጠባ ፣ የማበደር ዕድል ፣ ወዘተ ስለ አለው ፤ ሌሎች ባንኮች በምንም ዓይነት መልኩ ተወዳድረው ሊያሸንፉት ስለ እማይችሉ ፤ በሐገር ደረጃ ተወዳዳሪ ባንኮች እንደ አይፈጠሩ አድርጓል።

2.1.10 ካፒታል በማገት ጉዳት ያደርሳል

የእሚቀርብበት ክስ: ባንኩ የኢትዮጵያን የቁጠባ ሒሳብ ደንበኞች ቀኝ ግዛት ይዞ ነው የሐገር ኃብት እሚበዘብዘው።

- **ቀኝ አገዛዝ:** ቀኝ ገዢ ፤ በአብዛኛው ቀኝ የእሚገዛበት ምክንያት ፤ ቀኝ ገዝቶ በያዘው አከባቢ ፤ ከውድድር ነጻ የሆነ እና እርሱ በእሚወስነው መንገድ የእሚመረት እና የእሚሸጥ ዕቃ ፤ አምርቶ በመሸጥ ለእራሱ የኢኮኖሚ ጥቅም ለማስገኘት ነው። በእዚክ አንጻር ካየነው ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ፤ የቀኝ መንግሥት ተቋም ነው ማለት ይቻልል።
- **በዝባዥ የባንክ አሠራር:** ምክንያቱም ፦ መንግሥት በእሚከተላቸው በተለያዩ አሠራሮች ምክንያት ፤ የከተማውም የገጠሩም ኢትዮጵያዊ የእሚቆጥበውን ገንዘብ በብቸኝነት በመያዝ (ግማሹን) ፤ በጣም ዝቅተኛ የትርፍ መጠን ባላቸው የመንግሥት የምኞት ፕሮጀክቶች ላይ በማዋል ፤ ሐገራዊ ኃብቱ ፤ በውድድር ተሠራጭቶ ሐገር ከመጥቀም ይልቅ የመንግሥትን ምኞት እንዲያረካ ያደርጋል። ይኽም ዓይነተኛ የቀኝ ግዛት አካኼድ ነው ፤ ልዩነቱ ፦ ቀኝ ገዢዎች ይኽን ዓይነቱን ውድድር አልባነት እራሳቸውን ለማበልጸግ ሲጠቀሙበት ፤ የእኛ ሐገር ዓይነት ልማታዊ መንግሥታት ደግሞ ከትርፍ ይልቅ ኪሣራ ለእሚያመጣው ምኞታዊ ልማታዊ ፕሮጀክቶች ይጠቀሙበታል።

2.1.11 ለፖሊሲ ማበደር ያስከተለው የትርፍ መቀነስ

የእሚቀርብበት ክስ: ባንኩ ከገበያ ዋጋ በታች ለፖሊሲ ፕሮጀክቶች ስለ እሚያበድር ትርፋማነቱ ይቀንሳል

- **ትርፍ ቅናሽ:** በአማካይ ሲታይ የንግድ ባንክ የማበደሪያ ወለድ 14.5% ሲሆን ፤ የሌሎቹ የግል ባንኮች አማካይ የማበደሪያ መጠን ደግሞ 17% ነው። በኹለቱ መካከል ያለው ልዩነት የ2.5% በመሆኑ እና ጠቅላላ ባንኩ ያበደረው ገንዘብ መጠን 1,073,046,300,000 ወይንም አንድ ትሪልየን አከባቢ በመሆኑ ፤ ባንኩ ለመንግሥት ያበደረውን ብድር በገበያ ዋጋ ለግሉ መስክ ቢያበድር ፤ የትርፍ መጠኑ ቢያንስ በ40% ካልሆነም በ110% ሊጨምር ይችል ነበር።

- **የባከነ ዕድገት:** ይኸም ማለት ፤ የባንኩን ትርፍ በግማሽ ከመቀነስ ባሻገር ፤ በሐገሪቱ ውስጥ ሊፈጠር የሚችል እና በባንኩ የብድር ፖሊሲ ምክንያት ያልተፈጠረ ከፍተኛ የኃብት መጠን መኖሩን እና ባንኩ የሚከተለው የብድር ፖሊሲ የሐገሪቱን የጂዲፒ (GDP) ዕድገት እንደ ጎዳ ያሳያል።
- **ውጤቱም:** ኋላ ቀር ፣ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ግብርና ከፍተኛ የኢኮኖሚው አካል የሆነበት እና ከ50 በላይ ጥረት በኋላ እንኳን ኢንደስትራላይዝ መሆን ያልቻለ ሐገር ነው።

የክስ ማጠቃለያ : የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንደ ስሙ የንግድ ባንክ ሳይሆን ከፍተኛ መጠን ያለው ሐገራዊ የቁጠባ ኃብት ወስዶ ፤ በቅጥር የማሕበራዊ ሴፍቲ ኔት ግልጋሎት እየሰጠ ፤ በጣም ዝቅተኛ ምርታማነት ባላቸው ሠራተኞቹ አማካኝነት ፤ ዝቅተኛ ምርታማነት ላላቸው የመንግሥት ፕሮጀክቶች በርካሽ እያበደረ ፦ የእራሱን ትርፋማነት የሚቀንስ ፣ በልማታዊነት ስም አክሳሪ ለሆነ መንግሥት ርካሽ ብድር የሚያበድር ፣ በእዚኽም ኃብት የሚያባክን ፤ ኪራይ ሰብሳቢ እና ጥገኛ ፤ የተበላሸ የመንግሥት የቅጥር እና የልማት ፖሊሲ ማስፍጸሚያ ነው።

3 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በገበያ ቢሠራ

ለማስቀመጥ እንደ ተሞከረው ፤ ምንም እንኳን ትርጉም ያለው የፖሊሲ ወይንም የፅንሰ ኃሳብ ክርክር ማድረግ ቢቻል ኖሮ ፤ ገበያን ተጠቅመው የዘመናዊነት ማማ ላይ እንደ ወጡት እንደ እንግሊዝ ፣ እንደ አሜርካ ፣ እንደ ቺሊ ፣ እንደ ፖላንድ ፣ እንደ ሲንጋፖር ፣ ወዘተ ኹሉ ኢትዮጵያም በተሻለ ፍጥነት እና ጥራት የዘመናዊነት ማማው ላይ መውጣት ትችላለች ብሎ ማሳየት ይቻል ነበር።

ሆኖም በሐገራችን ካለ ደካማ የጽንሰ ኃሳብ ውይይት የማድረግ ባሕል ፣ ከነባራዊ ስረዓት ለውጥን የመግፋት ዝንባሌ ፣ ከጥቅመኝነት እሳቤ እና ከፅንሰኃሳባዊ ክርክሮች መሠረታዊ ውስብስብነት የተነሳ በእዚኽ መልኩ ሐገራዊ መግባባት መፍጠር አልተቻለም።

ከእዚኽ የተነሳ ፤ ኢትዮጵያ የተሳሳተ የፖሊሲ መንገድ በመምረጥ ፤ ወድቃ ከስህተቷ ለመማር ተገዳለች።

እሚያሳዝነው ፤ የግዜያዊ ጥቅመኝነት ፣ አንጻራዊ ስኬት ፣ አጉል የርዕዮተ ዓለም ጀብደኝነት ፣ ወዘተ ተዳምረው ፤ ውድቀትንም ውድቀት ብሎ መፈረጅ ያለመቻል ችግር የሐገራችን የፖለቲካ አመራሮች ችግር በመሆኑ ፤ በእየ ግዜው የእሚመጣው የኢትዮጵያ ፖለቲካ አመራር የሠራው እንጂ መሥራት ያለበት ነገር ግን ሳይሠራው የቀረውን ሥራ ማየት ተስኖታል።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ ኢትዮጵያ በጽነሰ ኃሳብ ትንተና ፤ ሳትወድቅ መማር ሳይሆን ወድቃ እንኳን መማር ያቃታት ሐገር ነው የሆነችው።

ምንም እንኳን ይኽ ከሞላ ጎደል የአብዛኛው ፖለቲከኛ ባሕሪ ነው ሊባል ቢችልም ፤ እንደ ኢትዮጵያ ያለ መሠረታዊ የሆነ ዘመናዊነትን የእሚሸከም የመዋቅር ለውጥ በእሚያስፈልግበት ሐገር ፤ መዋቅራዊ ሽግግርን የእማያመጣ የጥገናዊ ለውጥ እየተኩራሩ መኖር ፤ መሪዎቹንም ሐገርንም የእሚያጠፋ ፤ ከፍተኛ ስህተት ነው።

እንደ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለእዚኽ ዓይነተኛ ምሳሌ ያለ አይመስለኝም።

ሐገርን ከማዘመን አንጻር ፤ የተረከቧትን ኢትዮጵያ ፍጹም በመለወጥ ከተመዘነ ፤ ከእሳቸው በፊት እና ከእሳቸው በኋላ የነበረ የትኛውም የኢትዮጵያ መንግሥት እሚወዳደራቸው ያለ አይመስልም።

በፖለቲካው ብንወስድ ፦ ዘመናዊ ሕገ መንግሥት ያስተዋወቁ ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ ፓርላማ ያስተዋወቁ ፣ የፍትሕ ስረዓትን ከፍትኃ ነገሥት ወደ ፍትኃ ብሔር የለወጡ ፣ የጠቅላይ ምኒስትርነትን እና የመንግሥትን ካቢኔ በዘመናዊ መንገድ ያዋቀሩ ፣ የሐገርን መከላከያ እና ደህንነት በማዘመን በመሠረታዊነት ፊውዳላዊ የገበሬ ጦር የነበረውን በመቀየር ፦ አየር ኃይል ፣ ሜካናይዝድ ብርጌዶች ያሉት ምድር ጦር ፣ ባሕር ኃይል ፣ ዘመናዊ የጦር ትምሕር ቤት ፣ ወዘተ ያለው ቋሚ ዘመናዊ መከላከያ ሠራዊት አድርገው የገነቡ ፣ ወዘተ በአጠቃላይ ለእልፍ ዓመታት ፊውዳላዊ የነበረውን የኢትዮጵያ መንግሥታዊ አወቃቀር ዘመናዊነት ያላበሱት ኃይለ ሥላሴ ናቸው።

በኢኮኖሚው ብንወስድ ፦ ዘመናዊ የገንዘብ ስረዓት ፣ ባንክ ፣ ዩኒቨርስቲ ፣ ጥርጊያ መንገድ ፣ ሐገር አቋራጭ የባቡር እና የመኪና ትራንስፖርት ፣ ዘመናዊ እርሻ ፣ ዘመናዊ ትምሕርት ፣ የአክስዮን ኩባንያዎች ፣ ፋብሪካዎች ፣ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እንደ ኢትዮጵያ ቴሌኮምንኬሽን ያሉ አንጋፋ ቴክኖሎጂዎችን እና መሥሪያ ቤቶች ፣ ወዘተ የገነቡት ኃይለ ሥላሴ ናቸው።

ስለ እዚኽ ፦ በተረከቧት እና ባስረከቧት ኢትዮጵያ መካከል የብዙ ኪሎሜትር ልዩነት አለ። በእዚኽ ረገድ ፦ አይደለም ብልጽግና ፤ ኢሕአዴግ እና ደርግም አይወዳደሯቸውም።

ከእርሳቸው በፊት የነበሩ ነገሥታትም ፤ ሐገር በማቆየት ትልቅ ሥራ ሠርተው ሊሆን ይችላል ፤ ሐገር በማዘመን ግን ከኃይለ ሥላሴ አይወዳደሩም።

ይኽ ኹሉ የኃይለ ሥላሴ ስኬት ግን ፤ ኢትዮጵያን ኢንደስትርላይዝ ማድረግ አልቻለም።

ኃይለ ሥላሴ የሠሩት ሥራ ካልሠሩት አንጻር ሲነጻጸር ፤ ያልሠሩት በብዙ እጥፍ ይበልጥ ስለ ነበር ፤ ምንም እንኳን ይኽን ዓይነት ታላቅ ሥራ ቢሠሩም ፤ መጨረሻው የእርሳቸውም የሐገሪቱም ውድቀት ነው የነበረው።

እምንወድቀው ጉድለታችን ሲበዛ ነው። ስኬት ቢኖረንም ፤ ጉድለታችን ከስኬታችን ሲበዛ እንወድቃለን።

ስለ እዚኽ ፦ ፖለቲከኛም ሐገርም ፤ ስኬቱን እየቆጠረ ማንቋረር ሳይሆን ያለበት ፤ ጉድለቱን እያሰበ እርሱን ለመሙላት መሥራት ነው ያለበት።

እንግዲኽ ኃይለ ሥላሴ ምን አጎደሉ ከተባለ ፦ ሕገክራሲን እና ከአምባገነንነት ወደ ምርታማነት የእሚሉትን ኹለቱንም መጽሐፍ እንዲያነቡ ልጋብዝ እንጂ እዚኽ ላብራራው ብሞክር ከእዚኽ ጽሑፍ አጀንዳ እወጣለኹ።

ዋናው ቁም ነገር ግን ፤ በኢትዮጵያ ሐገር ከማዘመን ወይንም ኢንደስትራላይዝ ከማድረግ አንጻር ፤ አይደለም በምክር በመከራም ልንማር አልቻልንም።

ከእዚኽም የተነሳ ፦ የኃይለ ሥላሴን ከጨመርን ከ100 ዓመት የስልጣኔ ሙከራ በኋላ (ቆጠራውን ከደረግ ከጀመርን ከ52 ዓመት በሁላ) ከትውልድ ትውልድ መቀያየር በኋላ እንኳን ፤ በእምንከተለው የተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት ኢንደስትራላይዝ ማድረግ አቅቶን ፤ ዛሬም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከ33% ኋላ ቀር ግብርና ሲሆን የኢንደስትሪው ድርሻ ከ4% በትንሽ ቢበልጥ ነው ፤ እርሱንም አክሳሪ የሆነ እና በከፍተኛ የመንግሥት ድጎማ እና ድበቃ ነው እዚኽም የደረሰው።

ትልቁ ችግር ግን ይኽን ውድቀት ፤ ውድቀት ብለን መረዳት እንኳን ያቃተን ፤ ከምክር ሳይሆን ከውድቀቱ እንኳን መማር እማይችል ጉድ ሆነናል።

ለእዚኽም አንዱ ምክንያት ደግሞ ፦ ለምሳሌ ፦ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን እንደ ማሳያ ብንወስደው ፤ ባንኩ በእሚያወጣው ዓመታዊ ሪፖርት ፤ በ2016 የበጀት ዓመት 22 ቢልየን ብር (**22,023,323,313**) የተጣራ ትርፍ አተረፍኩ ፤ ይኽ ደግሞ በ2015 ካተረፍኩት 17 ቢልዮን ብር የተጣራ ትርፍ (17,436,631,798) አንጻር የ26% ጭማሪ አለው ወይንም በ2015 የበጀት ዓመት 17 ቢልየን ብር (17,436,631,798) የተጣራ ትርፍ አተረፍኩ ፤ ይኽ ደግሞ በ2015 ካተረፍኩት 16 ቢልዮን ብር የተጣራ ትርፍ (16,492,751,161) የ5% ጭማሪ አለው ብለን ፤ በስኬቱ የእምንፍነከነክ በመሆናችን ነው።

በእርግጥም በእዚያ መልኩ ብቻ ካየነው ፤ ምን አልባትም ፤ ንግድ ባንክ በዓለም ላይ አሉ ከእሚባሉ እንደ ስታንዳርድ ባንክ ወይንም ሲቲግሩፕ (Citigroup) ባንክ ፤ አንጻር እንኳን ትርፋማ እና ስኬታማ ባንክ ይመስላል።

ዕውነታው ግን ፤ ንግድ ባንክ ፤ ከእነ እዚኽ የዓለማችን ንፍሊሞች ጋር የተወዳደረው ፤ ንፍሊም ስለ ሆነ ሳይሆን ፤ ከእላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው ፤ ዓይነተኛ ኪራይ ሰብሳቢ በመሆኑ ፤ በልማታዊነት ስም ፤ የሰበሰበውን ግማሽ የእሚሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ የቁጠባ ገንዘብ ዜሮ ወይንም ትንሽ ወለድ በመክፈል ከተቀበለ በኋላ ፤ ምክር ቀርቶ መከራ ያላስተማራቸው የኢትዮጵያ ልማታዊያን ለነደፉት ከሳሪ የልማት ፕሮጀክቶች ብሩን በርካሽ በማበደር እና እነ እዚኽ ፕሮጀክቶች ቢከስሩ እንኳን ብድሩን እያሽከረከረ እና ወደ መንግሥት በንድነት እየቀየረ ኪሳራምነቱን ስለ እሚደብቅ ፤ በእዚኽ ላይ ግብር ቀንሶ ስለ እሚከፍል ፣ ወዘተ ነው።

ባንኩ በእዚኽ ኺደት ግን ፤ መተንፈስ እማይችል በርጫም ሆኖ ፤ ተራራ እንደ እሚወጣ አትሌት የመምሰል ችግር ብቻ አይደለም የተያዘው ፤ ይልቁንም ፦ የሐገሪቱ ዘመናዊ የገንዘብ ስረዓት ግማሽ በመሆኑ ፦ በእሚከተለው የተባላሸ የባንክ አሠራር ፤ የሐገሪቱን ዕድገት ፤ በእዚያም ከግብርና መርነት ወደ ኢንደስትሪ መርነት የእሚደረገውን ሽግግርም እያመከነ ያለ ነው።

ምንም እንኳን ከፍተኛውን ብድር ማለትም ፤ ለምሳሌ ፦ በ2023/2024 52% በሙቶ ለኢንደስትሪ መስክ ነው ያበደርኩት ስለ እዚኽ ፤ ለኢትዮጵያ ኢንደስትራላይዜሽን ትልቅ ሚና እየተጫወትኩ ነው ቢልም ፤ ኢኮኖሚው እና ሳይንሱ ግን አንተ ጥገኛ ክራይ ሰብሳቢ ፤ ገንዘብ በኢንደስትሪ መስክ ላይ በፖሊሲ በማፈሰስ ኢንደስትራላይዜሽን ማምጣት አትችልም ብሎ እያለው ነው።

በባንኩ የ2023/2024 ዓመታዊ ሪፖርት መሠረት ፤ ገበያው እና የኢኮኖሚው ሳይንስ ባንኩን ፦

- በጣም ዝቅተኛ የብድር ከፋይነት ደረጃ ላለው መንግሥት ከፍተኛ መጠን ያለው ርካሽ ብድር በማበደር የሐገሪቱን የዋጋ ግሽበት ስለ አናርክ ፥
- በሐገሪቱ ባለው በጠቅላላው የተበላሸ የፖሊሲ ምህዳር እና የውጭ ምንዛሪ ችግር ፤ የውጭ ሐገር ንግድ የመክሰር ደረጃው በእሚያስደነግጥ መልኩ 21% እንዲደርስ በማድረግ ውስጥ ስለ ተባበርክ እና በእዚኽ መልኩ እጅግ ከፍተኛ የመክሰር አደጋ ላለበት መስክ ቢልዮኖች ስለ እምታበድር ፥

- የኢትዮጵያን ሕዝብ ግብር ፣ ቁጠባ እና የውጭ አበዳሪዎችን ብድር እንዲኹም ድጎማ እየወሰደ የተበላሸ ብድርህን ገዛው በማለት መልሶ በቦንድነት በእሚሸጥልህ መንግሥት ተማምነህ የተባላሹ ብድሮችህን እየወሰድክ ወደ መንግሥት ቦንድ በመለወጥ ፤ ውድቀትኽን እና ኪሳራህን ስለ እምትደብቅ እና በእዚኽም በሐገሪቱ ገንዘብን ጨምሮ የብዙ ሸቀጦችን ዋጋ ስለ አዛባኽ፥

ሐገሪቱ አሁን ባለችበት ኹኔታ ፤ ለግብርና እና ለኮንሲውመር (Consumer) መስክ እንጂ ለማንፋክቸሪንግ አትመችም ብሎ እየነገረው ፤ በሳይንስ ሳይሆን ፤ ምክር ቀርቶ መከራ በእማይመክራቸው በልማታዊያኑ የፖሊሲ ምኞት ስለ እሚመራ ፤ 52% የእሚሆነውን ብድሩን 10% የመበላሸት እድል ላለው የማኑፋክቸሪንግ መስክ በማበደር ፤ ብዙ ቀዳዳ ባለው ባልዲ ውስጥ ውኃ ሞላለው የእሚል ባንክ ነው የሆነው።

በእዚኽም ንግድ ባንክ በገበያ ቢሠራ በእሚለው ክፍል ፤ ይኽን መልክ ያለው ያኃብት ማትነኛ እቶን የሆነውን ንግድ ባንክን ፤ አሁን ካለበት የቅጥር ሴፍቲኔትነት እና የመንግሥት የቅዠት ፕሮጀክቶች ፋይናንሰርነት አውጥተነው ወደ ንግድ ባንክነት ወይንም ከልማታዊነት ወደ ገበያ እንዴት ልናሸጋግረው እንደ እምንችል አስቀምጣለኹ።

ምክንያቱም :- ለምሳሌ :- በእዚኽ https://documents1.worldbank.org/curated/en/772161468782107741/pdf/Finance-and-the-sources-of-growth.pdf የወርልድ ባንክ ጥናት መሠረት ፤ በአንድ ሐገር ውስጥ ብድር የእሚሰጥበት አግባብ (በገበያ ይኹን ወይንስ በመንግሥት የፖሊሲ ውሳኔ) በአንድ ሐገር የኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው።

ከዓለም ባንክ የእሚገኙ መረጃዎች እንደ እሚያመለክቱት :- ለግሉ መስክ የእሚቀርበው የብድር አገልግሎት ሲጨምር ፤ ካፒታል ይበልጥ ትርፋማ በእሚሆንበት ቦታ ላይ እንዲውል ስለ እሚያደርግ የሐገርን ጠቅላላ የማምረት አቅም ወይንም ጊዲፒ (GDP) እንደ እሚያሳድግ ነው።

አኹን ባለው ተጨባጭ ኹኔታ ግን ፤ የኢትዮጵያን ንግድ ባንክ ብቻ እንኳን ከተመለከትን (ምክንያቱም :- የግል በእሚባሉት ባንኮች እራሱ ብድር በገበያ ብቻ እየተወሰነ አይደለም ፤ የተለያየ መልክ ባላቸው የመንግሥት ጣልቃገብነት ምክንያት) ፤ የሐገሪቱን ግማሽ ብድር የመስጠት አቅም ያለው ይኽ ባንክ ፤ ከ80% በመቶ በላይ የእሚሆነውን ብድር ፤ በገበያ ሳይሆን የመንግሥትን የፖሊሲ አቅጣጫ ተከትሎ ስለ እሚያከፋፍል ፤ ብድር ወይንም ካፒታል ይበልጥ ትርፋማ ከሆነበት ይልቅ የመንግሥትን ምኞት በእሚያረካበት እየዋለ በመሆኑ ፤ የካፒታል ብክነት በእዚያም የሐገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያደረሰ ነው።

ምክንያቱም :- ባንኩ ብድሩን ለበለጠው አትራፊ/አምራች መስክ ባለማበደሩ ፤ ሐገሪቱ ግብዓት እና ጉልበትን ወደ ኃብት የእምትለውጥበትን ኺደት እያዳከመ ነው።

አንድ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ደግሞ ፤ የሐገሪቱን ምርታማነት ወይንም ግብዓትን እና ጉልበትን ወደ ኃብት የእምትለውጥበትን መንገድ በማሻሻል ፤ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱን ካላሻሻለ ፤ ማነቆ ሆኗል ማለት ነው።

ደጋግሞ ለማለት እንደ ተሞከረው ፤ ንግድ ባንክ አላተረፈም ወይንም የሐገርን ኢኮኖሚ አላገለገለም አይደለም ፤ ይልቁንም ማትረፍ ከእሚገባው እና የሐገርን ኢኮኖሚ በማገልገል ማሳደግ ከእሚገባው አንጻር ፤ በአግባቡ ሚናውን ስለ አልተጫወተ ውጤቱ ፦ እንደ አቆጣጠራችን ከ100 ወይንም ከ52 ዓመት የዘመናዊነት ትግል በኋላ ኢትዮጵያ ዛሬም የኋላ ቀር ገበሬ ሐገር ነች።

ቀላል የእማይባሉ ከኢትዮጵያ ያነሰ ታሪክም አቅምም ያላቸው ሐገራት ግን ከ20 እስከ 40 ባለ ወይንም በአማካኝ በ30 ዓመት ውስጥ ኢንደስትራላይዝድ ሆነዋል።

ስለ እዚኽ ፦ ገበያው ብድር ነው ያጣው እንጂ ብድር ውስዶ ትርፋማ የመሆን አቅም አለው የእሚል ዕምነት ከተያዘ (If we hold that there is a credit absorptive capacity in the private sector) ፤ በእሚከተለው መንገድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ከልማታዊነት ወደ ገበያ መርነት ከለወጥነው ፦

- የትራፋማነት መጠኑን መጨመር
- የመንግሥትን የግብር ገቢ መጨመር ብቻ ሳይሆን

የሐገሪቱንም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መዋቅራዊ ለውጥ በእሚያስከትል መልኩ ማሳደግ ይቻላል።

በመሆኑም ፦ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ከልማታዊነት ወደ ገበያ ለማዞር የእሚከተሉት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ ፦

3.1 50% የባንኩን ድርሻ ከትርፍ የመካፈል መብት ጋር ለትልቅ የውጭ ባንክ መሸጥ

- **አስፈላጊነቱ:** በእዚኽ መልኩ የባንኩን 50% ድርሻ ከእነ ትርፍ የመጋራት መብቱ ጋር አብሮ ፤ ለተመረጠ ትልቅ የውጭ የግል ባንክ መሸጥ ፤ የግል ባለኃብቱ ባንኩ ውጪ እንዲቀንስ እና ተወዳዳሪነቱን እንዲጨምር ስለ እሚወተውተው ፤ የባንኩን ደረጃ ያሻሽለዋል ፤ አብሮም የዕውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርም እንዲመጣ ያደርጋል።

- **ውጤቱ:** የግል ባለኃብት 7.8% ገደማ የብድር የመበላሸት ዕድልን ወይንም 89 ሺ ሠራተኛን እሺ ብሎ አይቀበለም። የግል ባለኃብቱ የባንኩን ውጪ እና ስጋት ቀንሶ ትርፋማነቱን ለማሳደግ ሲወተውት ፤ ባንኩ የቅጥር ሴፍቲ ኔት ከመሆን ወደ እሴት ፈጣሪ ባንክነት ይሸጋገራል።

3.2 ባንኩ በሐገሪቱ የቁጠባ ሒሳብ ላይ ያለውን የበላይነት በሕግ መቀየር

- **አስፈላጊነቱ :** የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከ30% በላይ የሆነውን የገንዘብ እንቅስቃሴያቸውን በንግድ ባንክ በኩል እንደ አያደርጉ በመከልከል እና 70% የእሚሆነው የገንዘብ እንቅስቃሴያቸው ለግል ባንኮች እንዲከፈት በማድረግ ፤ በሐገሪቱ ውስጥ ደልዳላ የመወዳደሪያ ሜዳ መፍጠር ይገባል።

- **ውጤቱ:** ይኽ አካኼድ ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፤ የመንግሥት ገንዘብ በዜሮ ወይንም በትንሽ ወለድ እቅፉ ውስጥ እንዲወድቅለት የእሚያደረግለትን የኪራይ ሰብሳቢ አካኼድ ያስቀራል። ያን ግዜ ንግድ

ባንክ ከሌሎች ባንኮች ጋር የቁጠባ ገንዘብ ለማግኘት ጥሩ ወለድ በመክፈል እና የአገልግሎት ጥራት በመስጠት ስለ እሚወዳደር ፤ አሁን ደካማ ከሆነው በሠራተኛ ካለው ዝቅተኛ ምርታማነት (**Productivity per Employee**) በመውጣት ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ይሆናል።

3.3 የባንኩ ቦርድ ነጻ እና ገለልተኛ እንዲሆን 50% በግል ባለ ኃብቶቹ እንዲሰየም ማድረግ

- **አስፈላጊነቱ:** የባንኩ ቦርድ በመንግሥት ምርጫ ብቻ የእሚያዝ ከሆነ ፤ የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚን ጨምሮ ሌሎች ወሳኝ የባንኩ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ፤ በፖለቲካ ፍላጎት የእሚሾሙ እና ከትርፋማነት ይልቅ ለመንግሥት የእሚታዘዙ እንዲሆኑ ስለ ሆነ ፤ የቦርዱን አባላት 50% በግል እንዲሰየሙ ማድረግ ፤ ወደ ፊት መኬጃው መንገድ ትርፋማነት እንጂ የመንግሥት አደርባይነት እንደ አይሆን ያደርጋል።
- **ውጤቱ:** ለምሳሌ ፦ ባንኩ 52% በመቶ የእሚሆነውን ብድሩን በመንግሥት ስለ ታዘዘ ብቻ ለማንፋክቸሪንግ አያውልም ፤ ይልቁንም የትኛው መስክ ዝቅተኛ ሪስክ እና ከፍተኛ ትርፋማነት አለው ብሎ ፤ ከፍተኛ ትርፋማነት እና ዝቅተኛ ሪስክ ላለው መስክ በማበደር ፤ የእራሱን ትርፋማነት ያስድጋል ፣ የስጋት መጠኑን ይቀንሳል ፣ በእዚያ ኺደትም የሐገርን ጠቅላላ ምርታማነት ያሳድጋል።

3.4 ባንኩ በዓለም ላይ ካሉት አራት ዋነኛ ኦዲተሮች በአንዱ ኦዲት እንዲደረግ በማድረግ የባንኩን ግልጸኝነትን ማረጋገጥ

- **አስፈላጊነቱ:** ባንኩ ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ እንደ ኧርነስት ያንግ ወይንም ዴልዮት (**Deloitte, PricewaterhouseCoopers (PwC), Ernst & Young (EY), and KPMG,**) ባሉ የዓለማችን ትልልቅ አራት የኦዲት ፈርሞች በአንዱ ኦዲት ካልተደረገ ፤ የተበላሹ ብድሮቹን ፤ በተለያዩ የአካውንቲንግ ትሪኮች ሊደብቃቸው እና የድሮውን የበግ ለምዱን ሊቀጥልበት ይችላል።
- **ምክንያት:** በእዚኽ መልኩ ግልጸኝነት ካልተረጋገጠ ውጤታማነት ሊረጋገጥ አይችልም።

3.5 ከፍተኛ የባንኩ ተበዳሪ የሆኑትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለግል መሸጥ

- **አስፈላጊነቱ:** ባንኩ ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች በፖሊሲ እያበደረ ሲከስሩ ፤ ከሰሩ ብሎ ድርጅቶቹን ወርሶ ከመሸጥ ይልቅ ፤ መልሶ ለመንግሥት በቦንድ መልክ በመሸጥ ፤ የተበላሹ ብድሮችን አቅፎ አቅሙን የእሚያዳክምበትን አሠራር ያስወግዳል። እንደ ስኳር ኮርፖሬሽን እና የኢንደስትሪ ፓርኮች ያሉ መንግሥታዊ የልማት ድርጅቶችን በመሸጥ ፤ ከእዚያ የእሚገኘውን ገቢ ፤ በባንኩ ሒሳብ ላይ በኮርፖሬት ቦንድነት ተመዝግቦ የእሚገኘውን ወደ **633.8 ቢልየን** ብር ያጸዳበታል።
- **ውጤቱ:** በእዚኽ መልኩ የመንግሥትን የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ማዞር ኹለት ጥቅም አለው ፦
    - አንዱ ከፍተኛ የሐገር ኃብት ወይንም ካፒታል ፤ ዝቅተኛ የትርፋማነት እና ተወዳዳሪነት እያላቸው በመንግሥት ፖሊሲ ምክንያት ግን ብዙ ኃብት ይዘው ከተቀመጡ ድርጅቶች

በመውጣት ፤ የተሻለ ትርፋማነት እና ተወዳዳሪነት ላላቸው ሌሎች መስኮች እንዲውል ሲያስችል ፥

- ኹለተኛው ደግሞ እነ እዚኽ የልማት ድርጅቶች ፤ ቢከስሩ እንኳን ከሰሩ ተብለው ሳይዘጉ ኹል ግዜ ብድራቸው መክፈያ ግዜው እየተራዘመላቸው እና የክፍያው መጠን እየተስተካከለላቸው በሪስትራክቸሪንግ የተሸሸጉ ደካማ ድርጅት ከመሆን ወጥተው በምርታመነት ተወዳደረው ወደ መኖር እንዲመጡ ካልሆነም መስክ እንዲቀይሩ በማስገደድ ፤ የሐገር ኃብት እና ትኩረት ከምኞት ኢኮኖሚ ወደ ምርታማ ኢኮኖሚ እንዲሸጋገር ያደርጋል።

3.6 ባንኩ የመንግሥትን በንድ በገበያ የወለድ መጠን እንዲገዛ ማድረግ

- **አስፈላጊነቱ:** በባንኩ ሪፖርት መሠረት 64.5% የእሚሆነውን ብድር ባንኩ በርካሽ ወለድ ለመንግሥት በቦንድ ግዢ መልክ ያበደረው ነው። ባንኩ ከእዚኽ በኋላ ከመንግሥት የእሚገዛውን በንድ የእሚገዛው በርካሽ ሳይሆን በገበያው የወለድ መጠን ወይንም በአሁኑ በገበያ የገንዘብ ዋጋ **17%** ቢያደርገው ፤ ባንኩ ለመንግሥት የእሚያደርገውን ድጎማ ያቆማል ማለት ነው።
- **ውጤቱ:** ያን ግዜ መንግሥት ትክክለኛውን የመበደር ዋጋ ያውቃል። በእዚያም መንግሥት ብድር ሲወደድበት ፤ በርካሽ ብድር እንደ እሚያገኝበት ግዜ ፤ እየተበደረ ገንዘብን በምርታማ ሳይሆን በምኞት ፕሮጀክቶቹ ላይ የእሚያድፋፋበት ኹኔታ ስለ እሚቀር ፤ ገበያው ውጤታማ የካፒታል አከፋፋይ እንዲሆን ማድረግ ብቻ ሳይሆን ፤ የዋጋ ግሽበትን በመግታት ፣ ለምርታማ መስኮች በቂ ብድር እንዲኖር በማድረግ ምርታማነት ማሳደግ ፣ የሥራ አጥነት ቁጥር እንዲቀንስ ፣ ወዘተ ያደርጋል።

3.7 ከመንግሥት በንድ ግዢ የእሚገኝ ገቢ እንደ ሌላ ማንኛውም ዓይነት ገቢ የመንግሥትን የገቢ ግብር እንዲከፍል ማድረግ

- **አስፈላጊነቱ:** ባንኩ ከፍተኛ መጠን ያለው ፤ 64.5% የእሚሆነውን የጠቅላላ ብድሩን መጠን ፤ ከትርፉ ወለድ በእማይከፍልበት የመንግሥት በንድ ላይ ስለ አዋለው እና ከመንግሥት በንድ ግዢ የእሚያገኘውን ትርፍ ግብር ስለ እማይከፍልበት ፤ ባንኩ ትርፋማ ከሆነው በላይ ትርፋማ የሆነ እና በዕውነት ካለበት የስጋት ደረጃ በጣም ያነሰ ስጋት ያለበት ወይንም በሞያው ቋንቋ ካፒታል አዲኩዌሲው (Capital Adequacy Ratio - CAR) ከፍተኛ የሆነ ያስመሰለበት ነገር ይቀርና ፤ የባንኩ የትርፍ ኹኔታ እና የስጋት ደረጃ ትክክለኛ መጠኑን ይይዛል።
- **ውጤቱ:** ያን ግዜ ባንኩ ትርፋማነቱን በገበያ ወይንም በትክክለኛ ምርታማነት መሠረት ለማሳደግ እና የስጋት ደረጃውንም ለመቀነስ ሲጥር ፤ ገንዘብን ደካማ የብድር ከፋይነት ደረጃ ላለው መንግሥት ከማበደር ይልቅ በገበያ ተወዳዳሪ እና አምራች ለሆኑ መስኮች በማበደር ፦
    - ትርፋማነቱን በጤናማ መንገድ ያሳድጋል ፥
    - የስጋት ደረጃውን በጤናማ መንገድ ይቀንሳል ፥

- ብድርን ከመንግሥት ወደ ግል በማዞር ፤ እንደ አንድ አንድ ጥናቶች ፤ አንድ 1% ወደ ግል የዞረ ብድር እስከ 0.25% የእሚደረስ የጂዲፒ (GDP) እድገት እንዲያስከትል ሊያደርግ ይችላል ፥
- የዋጋ ግሽበት ይቀንሳል
- የሥራ አጥነት ቁጥር ይቀንሳል

3.8 ባንኩ መንግሥት በቅርቡ ካቋቋመው የዕዳ እና የንብረት አስተዳደር ኮርፖሬሽን (Liability and Asset Management Corporation - LAMC) ጋር ያለው ግንኙነት በሕግ መቋረጥ አለበት

- **አስፈላጊነቱ:** ይኽ የዕዳ እና የንብረት አስተዳደር ኮርፖሬሽን ፤ ንግድ ባንክ በተበላሸ አካኼዱ እየኼድ የእሚፈጥራቸውን ከፍተኛ መጠን ያላቸው የበሰበሱ/የተበላሹ ብድሮችን የእሚጥልበት ቆሼ ነው የሆነው። ንግድ ባንክ ለባቡር ኮርፖሬሽን ፣ ለስኳር ኮርፖሬሽን ፣ ወዘተ ተገቢውን ምርመራ እና ምዘና ሳያደርግ የመንግሥትን የፖሊሲ ግብ ለማሳካት ብቻ አክሳሪ ብድሮች ያበድራል ፤ ብድሩ ሲበላሽ እና ሲበሰብስ ፤ የንግድ ባንክ ቁመና እንደ አይበላሽ ፤ የዕዳ እና የንብረት አስተዳደር የተበላሸውን ብድር ቆሻሻ ይገዛዋል። ስለ እዚኽ ፦ የዕዳ እና የንብረት አስተዳደር ኮርፖሬሽን ፤ የንግድ ባንክ የተበላሸ ብድር ቆሻሻ መጣያ ነው። የእዚኽ ትልቁ ችግር ኹለት ነው ፦
    - **ባንኩ የተበላሹ ብድሮች** ወደ ዕዳ እና የንብረት አስተዳደር ኮርፖሬሽን ማዛወር ቻለ ማለት ብድር የወሰዱት ተቋማት ምርታማነት እና ትርፋማነት ተለወጠ ማለት ባለመሆኑ ፤ የኪሣራው ምንጭ አሁንም በሐገር ደረጃ በመቀጠል ፤ ካፒታል ያመክናል ፣ በሐገር ደረጃ የዋጋ ግሽበት እና የወለድ መጠን ያስወድዳል ፣ ሥራ አጥነት ያበራክታል ፣ ወዘተ
    - የዕዳ እና የንብረት አስተዳደር ኮርፖሬሽን የተበላሸ ብድር መውሰድ የእሚችለው ፦ በአንድም በሌላ መንገድ የሐገር ኃብትን ወስዶ ፤ እነእዚኽ የተበላሹ ብድሮችን በመሸፈን ነው። ለምሳሌ ፦ ለማቋቋሚያ ከመንግሥት ካዝና ወጥቶ የተሰጠውን ወደ 142 ቢልዮን ብር ፣ ወይንም መንግሥት በዴቭደንድ ክፍያ ከቴሌ ፣ ከአየር መንገድ ፣ ከንግድ ባንክ ራሱ ፣ ወዘተ የእሚያገኛቸውን ገቢዎች ፣ ወዘተ ተጠቅሞ በመሆኑ ፤ ተጨባጭ ኹኔታው በሐገር ደረጃ ኪሳራ ቢሆንም ፤ በቁጥር አክሮባት ግን ፤ ችግሩን ከባንኩ አንጻር የፈቱ በማስመስል ችግሩን በመንግሥት ብሎም በሐገር ጉያ ውስጥ ይደበቃል።
- **ምክንያት:** ንግድ ባንክ በከፊል ወደ ግል ቢዛወር እንኳን ፤ በእዚኽ መልኩ የተበላሹ ብድሮችን የእሚያጉርበት ሐገራዊ ተቋም ካለ ፤ ብድር ሲያበድር ተገቢውን ምዘና እና ምርጫ በማድረግ ጠንቃቃ ሊሆን አይችልም።

ክቡር ኢትዮጵያዊያን ፤ እናንተን እንደ አደባባይ ችሎት (ፎረም) አይቼ ፤ የንግድ ባንክ በልማታዊነት በመመራት እራሱን እና ሐገር ጎድቷል ፤ በገበያ ቢመራ ግን ራሱን ይበልጥ ጠቅሞ ሐገርን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት ኢንደስትራላይዝድ ለመሆን የእምታደርገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ያሳካል ብዬ ፤ የፅንሰ ኃሳብ ሳይሆን ፤ የውጤት ምዘና ላይ የተመሰረተ ክስ እና ሙግት አቅርቤያለኹ።

ክሴን ካዳመጣችኹ በኋላ ፤ ንግድ ባንክ በልማታዊነት ከእሚመራ ይልቅ በገበያ እንዲመራ እንደ እምትወስኑ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ተመሳሳይ ክስ እና ሙግት በተመረጡ ኹለት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ላይ በማቅረብ እስከ እምንገናኝ ፤ የእዚያ ሰው ይበለን በማለት ይኽን እጨርሳለኹ !